ዘነበ ወላ

# ልጅነት

ልቦለድ
2000 ዓ.ም

"አንተ ማነው ስምህ? አርፈህ ተማር ጥሬም ካለህ እረፍት ላይ ትደርስበታለህ"

ተረጋግተን መማር ልንጀምር ስንል፣ አከክ መላ አካላቱን የወረረው አንድ ቀጫጫ ልጅ በቀኝ እጁ ግራውን እያከከ "ስጠኝ?" ብሎ እከካም ግራ እጁን ዘረጋልኝ:: አካሉ ይቀፋል፣ አለማመኑ ያሳዝናል:: ቆንጥሬ ሰጠሁት::

"ሀ" አለ መምህሬ፤

"ሀ" አልኩ ባኮረፈ ድምፅ:: አንዴ መቃም አምሮኛል፣ ይህ መብቴ ግን በአለቃችን ሥልጣን ታግዷል::

"ሄ" ጋ ስንደርስ፤

መቃ በፍጥነት አጠገቤ መጥቶ ተቀመጠና "ፉንጋይ የምመ ክርህን ብትለማ ይሻልሃል:: ለጌታቸው ትንሽ አሹቅ ስጠው" አለኝ:: ቀና ብዬ ሳይ ጌታቸው መቃ ወንበር ላይ ተቀምጦ ያፈ ጥብኛል::

"አልሰጥም"

"አይ! ሰበብ ፈልጎ ይገርፍሃል፣ ያንበረክክሃል፣ በኩርኩም ይቆጋሃል:: የኔታ ደግሞ የሚሰሙት እሱን ብቻ ነው:: እኛም ፈርተን ጥፋተኛ መሆንህን እንመሰክራለን" አለኝና አሹቅ እንድ ሰጠው እጁን ዘረጋ::

በእንቢተኝነቴ ትከሻዬን ሰበቅሁ:: ለመቃ ግን ትንሽ ዘግኜ ሰጠሁት:: ተቀበለኝና እኩል ለእኩል አካፍሎ ለጌታቸው ገበረ:: የተቀረውን ለነዚያ ዘርዛራ ትንንሽ ጥርሶቹ አቀበለና ከካቸው:: አቆረጣጠሙ በአፌ ምራቅ እንዲሞላ አደረገኝ:: ሳይጣደፍና ሳይ ፈራ ቦታው ተመልሶ ተቀምጦ ፊደሉን አነሳ::

ጌታቸው በጣም በሽቆ መቃ የሰጠውን ጥሬ እየቃመ፣ አጠገቡ ያኖረውን አርጩሜ አንስቶ አንዴ ሾጥ አደረገኝ::

ጮኸኩ::

"ምንድነው?" የኔታ ቀና ሳይሉ ጠየቁ::

"ይህ አዲሱ ልጅ በደንብ አይማርም" እያለ ጌታቸው ለየኔታ እየተናገረ፣ በአኳኋኑ ገና አሳርህን አሳይሃለሁ በሚል ዛቻ አፈጠጠብኝ::

"ኧረ አንተ ልጅ ተው ተማር!" ብለው ገሰጡኝ::

ከግቢው ውጪ ከፍተኛ የጩኸት ድምፅ ተሰማ:: በሩ ተበርግዶ ተከፈተ:: ቦችራን እናቱ እማማ አሰለፈች በገመድ ጠፍረውት እየጎተቱት ገቡ:: ደንብሮ እንዳይፈረጥጥ ታላቅ እህቱ ገነት ትልቅ አርጩሜ ይዛ ከኋላ ተከትላለች::

እማማ አሰለፈች እርር ድብን እያሉ "ይኸው የኔታ፣ ይዘነው መጥተናል:: ይህ ዱር ቤቱ የሆነ ልጅ!" አሉ::

የኔታ ከበርጩማቸው ላይ ፍየል እንዳየ ነብር እመር ብለው ተነሱና "እህ! አንተ የዱር ድመት፣ በመጨረሻ ተገናኘን?"



ዘንቦ እንዳባራ ሁሉ የተማሪዎቹ ጩኸት ፀጥ ረጭ አለ:: ዓይኖቻቸው ተጎልጉለው ወጥተው ቦችራ ላይ አፍጠዋል:: እኔና አሹቄንም ረሳን:: የቦችራ ጩኸት አየሩን ሞላው:: ለማፈትለክ ይታገላል:: ለጋ ጉልበቱ በሦስት ሰዎች ተጠምዶ ሊቋቋም አልቻ ለም:: ንፍጡ፣ እንባውና ላቡ ፊቱን አርጥበውታል::

"ወይኔ ኡ! ኡ! ኡ! አንቺ ነሽ ያስያዥሺኝ አ!" ብሎ እህቱ ላይ አፈጠጠ::

"ፐ! ዱርዬው ተያዘ!" አለ ጌታቸው::

"ዱርዬ አልከው? የሰፈሬ ልጅ ነው እነግረዋለሁ!" አልኩ እየተቆጨሁ::

"ተይ አንቺ ቀጫጫ! ብታርፊ ይሻልሻል፤ አለበለዛ እጨ ፈልቅሻለሁ:: ደሞ ለዱርዬነቱ ምን ምስክር ያስፈልገዋል? ትም ህርት ቤት እሄዳለሁ እያለ ካምቦሎጆ አይደለም የሚውለው? ዛሬም እንደተለመደው ፓስቴውን እየበላ ሲሽሎከሎክ ተያዘ:: ተው ትንሽ አሹቅ ስጠኝ!?"

ትከሻዬን በእምቢታ ሰበቅኩ::

ቦችራ አሁንም የድረሱልኝ ድምፁን ያሰማል:: አካላቱ በአቧራ ተለውሷል:: ለማምለጥ ሲጣጣር ባልተሳካ ትግሉ ሰውነቱ ተላልጧል::

የኔታ ክንብንባቸውን አውልቀው ወንበራቸው ላይ አስቀ መጡ:: አለንጋቸውን አንስተው "እሺ የእኛ የዱር ድመት፣ የት ከረምክ?" ብለው ቃጡና ባለ ኃይላቸው በአለንጋቸው ዠለጡት::

እሪታውን አቀለጠው:: ተስፋ ሳይቆርጥ አሁንም ለማ ምለጥ ይታገላል:: እናቱና እህቱ ሳያላውሱ ይዘውታል:: እማማ አሰለፈች "የኔታ እግር እግሩን! አዎን እሱጋ! አይ፣ ከፍ አሉ:: እያዩ፣ ሰበብ ይሆንቦታል! አዎን አሁንም ዝቅ! ዝቅ" ይላሉ ሆዳ ቸው እየተሸበረ፣ ውጫዊ አካላቸው የተደሰተ እየመሰለ::

ከእኛ ጋር የምትማረው ታናሽ እህቱ ሂሩት ይህ ሁሉ ግርፊያ በወንድሟ ላይ ሲወርድ ስታይ ሳይነኳት ማልቀስ ጀመረች::

እኔ በማየውና መኖር በጀመርኩት አዲስ ሥርዓት ላይ ጥላቻ አደረብኝ:: ሽንቴ ወጠረኝ:: በግርግሩ መካከል እንዴት ማምለጥ እንዳለብኝ አብሰለሰልኩ:: ቦችራ ተሰማ ተይዞ ባይመጣ የዬኔታን አለንጋ የምቀምስበት ወቅት ደርሶ እንደነበር አስታ ወስኩ::

የሚመለከተውን ጭፍግ ሕይወት መቋቋም የተሳነው አንዱ ሕፃን ፊሱን ጡጥ! አደረጋት:: ሌሎቹ ዞረው አዩትና ሳቁበት:: ጭንቁን ያረገበው ሕፃን አጠገቡ ወዳለው ልጅ እየጠቆመ "እኔ አይደለሁም እሱ ነው የፈሳው" ሲል ተከራከረ:: ቢሆንም በእፍ ረት ከአፍ የወደቀ ጥሬ አከሏል::

ቦቸራ ተጠልፎ ወደቀ:: በተዘረረበት፣ በላዩ ላይ የሚወርደውን አለንጋ ለመቋቋምና ለመመከት እየሞከረ "የኔታ፣ ሁለተኛ አይለምደኝም! ሁለተኛ !..." ተማፀነ::

የታነቀ እውነቱን ይናገራል፣ ነገርግን የሚያምነው የለም እንዲሉ፣ የኔታ በአፀፋው አላኹበት:: "አሄሄ! እንተዋወቃለንኮ በቸራ! እባብ ለእባብ አለ... ሁሌም አንተ ወጥመድ ውስጥ ስትገባ ማምለጫ ጥበብህ ሁለተኛ አይለመደኝም ነች!" ብለው የበሉ የጠጡትን ያህል ገረፉት:: በአሰነዛዘራቸው የእማማ አስለፈችን ምክር ልብ ያሉ አይመስልም:: ጥምጥማቸው ወልቆ መሬት ተንከባለለ:: የተላጠ ድንች የሚመስለው መላጣ እናታቸው እርቃኑን ቀረ::

በዚህ ወቅት የሁሉም ትኩረት ቦቸራ ላይ መሆኑን አየሁና ሹልክ ብዬ ወጣሁ::

## ወደ ሐኪም ቤት

*"ልጆቻችሁ በእናንተ በኩል መጡ እንጂ ከእናንተ አልወጡም"*
*- ካሊል ጊብራል*

ወደ ሰፈሬ ለመመለስ መንገዱ ምንም አላሳሳተኝም:: ጠዋት አባቴ እንዳልሳሳት ባሳሰበኝ መሠረት ምልክት ባደረኳቸው ነገሮች መሪነት ሠፈሬ ተመለስኩ:: አበራ ወፍጮ ቤት አካባቢ ስደርስ ትምህርት ቤት ያልገቡትን የሰፈሬን ልጆች ከርቀት አየኋቸው::

ቀጢሳውና ሴምላል የጭቃ ብይ ሲጫወቱ፣ ቁልጭና ባሬቾ ቆመው ይመለከቱዋቸዋል:: እኔ እያለከለኩ አጠገባቸው ስደርስ ጨዋታቸውን አቁመው እንደ ልዩ ፍጥረት አፍጥጠው አዩኝ::

"ተማሪ ቤት ገብተህ አልነበረም?" አለኝ ቀጢሳው በመደነቅ እያስተዋለኝ::

"ወጣሁ!" አልኩ ቁርጥ ቁርጥ በሚል ትንፋሽ:: ከኋላዬ ማንም እንዳልተከተለኝ ዞሬ መንገዱን እየቃኘሁ::

"መቼ?"

"ድሮ::"

ሁሉም ሳቁ::

ሴምላል የተንጠለጠለ ንፍጡን ከአፍንጫው ላይ በእጅጌው እየጠረገ" ጠዋት እኮ ድሮ አይደለም:: ተማሪ ቤት የገባኸው ዛሬ ጠዋት ነው:: የወጣኸውም ዛሬ ነው" ብሎ አረመኝ::



"ለምን ወጣህ?" ብሎ ቁልጭ በንዴ ስሜት ብልጣብልጥ ዓይኑን ሳያረግብ ጠየቀኝ::

"ይጋረፋሉ:: ቦቸራን በገመድ ጠልፈው ሲገርፉት ሳይ ፈርቼ ሮጬ ወጣሁ" አልኳቸው፣ አኳኋኑ አሁን እንደሆነ ሁሉ እየዘገነነኝ::

"ቦቸራ ተያዘ?!" አለ ባሬቾ ደንግጦ::

"አዎን ተያዘ:: የኔታ ጠልፈው ጥለውት በጣም ገረፉት:: ሲገርፉት ጥምጥማቸው ተፈቶ ወደቀ:: ደግሞ መላጣ ናቸው፣ የተላጠ ድንች ይመስላል:: ሲገርፉት... ሲገርፉት... እሱ ደግሞ ሲጮኽ ሲጮኽ እማማ አስለፈች ቆመው ሲያስገርፉት... ጎሽ የኔታ ትንሽ ዝቅ... እያሉ ሲያስደበደቡት" አልኩና ልክ እሳቸው እንደሚጋረፉት አይነት አስር አስር ጊዜ መሬት ላይ ቃጣሁ::

"ሄደን በአጥር ቀዳዳ ሲገርፉት እንይ?!" አለ ቀጢሳው::

"መንገዱን ማን ያውቀዋል?" አለ ባሬቾ::

"ቃንጌ አሳየን?" አለ ሴምላል::

"እኔ? እምቢ !" አልኩና ወደ ቤቴ አፈገፈግኩ::

"ተወው! እኔ አውቀዋለሁ እንሂድ" አለ ቀጢሳው:: የጭቃ ብዩን ለመሰብሰብ እንኳን ጊዜ ሳይኖረው ወደ ቄስ ትምህርት ቤቱ አቅጣጫ መሮጥ ጀመረ:: ሌሎቹ ተከተሉት::

እየፈራሁ እየቸርኩ፣ ለወላጆቼ ምን አይነት ምክንያት ባቀርብ እንደምታመን እያብሰለሰልኩ ወደ ቤቴ ማዝገም ጀመርኩ:: እናቴ የቡና አተላ ልትደፋ ወጥታ ከርቀት አየችኝ:: እሱ ነው? እሱ አይደለም በሚል ስሜት እያጣራች ነው:: እኔ ቀስ እያልኩ እግሬን እየጎተትኩ ወደፊት እንፏቀቃለሁ:: እኔ መሆኔን ለየች:: መደነቅም መገረምም በገጽዋ ላይ ይነበብ ጀመር:: አተላውን በፍጥነት ደፍታ በቆመችበት፤

"ዜራሞ" ስትል አባቴን ተጣራች::

"ወይ !" ቤት ውስጥ ሆኖ መለሰላት::

"ና... ጉዳችንን እይ!" መሳቅ ጀመረች::

ከሸማኔ ጉርጓድ ውስጥ ባዶ እግሩን ቱር ብሎ ወጥቶ እንዳየኝ በሃፍረት ፈገግታ ፈዞ ቀረ::

"አላውቅልህም! እኔ እንጃ! መጥፎ ትምህርት ቤት ነው ያስገባኸኝ:: ይጋረፋሉ" አልኩ እየተጠጋሁት::

"ገና ከመግባትህ ምን አጥፍተህ አቀመሱህ?" አለና አፈፍ አድርጎ ተሸክሞኝ ወደ ቤት ገባን:: እያወረደኝ "እንዴ! ቂጥህን ምን አረጠበው?" አለና ቂጤን አዙሮ አየው::

"ሽንቱን ለቆት ነዋ! አፈር በሆንኩ! ምን አድርገህ ነው ይህንን ያህል ያሸበሩህ?!" አለችና አካላቴን ደባበሰኝ፤ በሽንት የረጠበ ልብሴን ማውለቅ ጀመረች:: ቦት ጫማዬም በሽንት ተሞልቷል::

"ይጋረፋሉ::"

"ምን አጥፍተህ?" አባቴ ጠየቀኝ::

## ባልና ሚስት

*"...ኧረ ይሻልሻል ይሻልሻል፣*
*አበበ ቢቂላ ያገባሻል፣*
*ጥላሁን ገሠሠ ይድርሻል*
*- ልጆች ሆነን ከዘፈንነው*

እናቴ ላይ -አንድ ትልቅ ጠባሳ አለ፡፡ እማማ ማሚቴ ናቸው ድሮ የፈነከቱኝ፡፡ አሁን ድንገት ይህንን ጠባሳ ስነካው በትዝታ ፈረስ ወደኋላ ሽምጥ ጋለብኩ፡፡

ከጓደኞቼ ጋር ዕቃ ዕቃ እንጫወት ነበር፡፡ ይህ ጨዋታ ሴቶችንም ይጨምራል፡፡ እኔን ባል፣ መቅደስን ሙሽራ አደረጉ፡፡ የእናቷ የእማማ ማሚቴ ሻሽ እናቷ ላይ እንደ ቬሎ በከር ሸብ ተደርጎ ቁልቁል ተለቆ አጊጣለች፡፡ አበባም ታቅፋለች፡፡ በእኔ ቁምጣ ላይ ምንም አይነት ለውጥ አልተደረገበትም፡፡ በግራ ትከሻዬ ላይ ያለው ውልቅ ውልቅ እያለ ያስቸግረኝ የነበረው ማንገቻ ከቀኙ ማንገቻዬ ጋር በልጥ ወደ ኋላ ታሰረ፡፡

እኔና መቅደስ ጎን ለጎን ተቀምጠን እጆቻችን ተቆላል ፈዋል፡፡ ሚዜዎቻችን በግራም በቀኝም ከአጠገባችን ተቀም ጠዋል፡፡ አበረ ሻቃ የቆርቆሮ ከበሮውን እየደለቀ "ሙሽርዬ ሙሽር አበባ፣ ይዘህ በጊዜ ግባ!" እያለ ያዜማል፡፡ የከበሮ አመ ታቱም ሰምሮለታል፡፡

"ኃይለሥላሴ ይሙት! የማታጨበጭቡ ከሆነ ከዚህ እናባ ርራችኋለን!" እያለ ሲሳይ ጉቢጥ ሕፃናቱን ያስጠነቅቃል፡፡ "ኃይሉ ዶሮ አታጨበጭብም?!"

ይጥና በዚያ ጆሮ በሚበጥጥ ድምፁ አዝማቹን ካላወርድኩ ብሎ ከዜማው ጋር ግብግብ ገጥሟል፡፡ የድምፁ አወራረድ ባይስምርለትም ፍንደቃው ከልክ በላይ ሆኖ "ሙሽርዬ..." እያለ ሲያላዝን፣ አብነት ባሪያው በእወራረዱ ተበሳጭቶ በካልቾ ለጋና ዝም አሰኘው፡፡

ይጥና ሲነጫነጭ ባሪያው ፈገግ ብሎ በእፍረት አፍንጫ ውን እያላበው "ምሳው እስኪዘጋጅ አሁን ሽርሽር ሄደው ይምጡ" አለና እየተሽኮረመመ ሃሳብ አቀረበ፡፡

ኃይሉ ዶሮ ከሸቦ የሠራትን የሙሽራ መኪና እያጠማዘዘ የኋሊት ሄደና ሙሽሮቹን ሊጭነን አዘጋጀ፡፡ ጡሩንባም የሞተር ድምፅም እያሰማ አጃቢዎች ገለል ብለው መንገድ እንዲለቁለት ያስጠነቅቃል፡፡ የተበጠሰ ማንገቻው እንዳይጠልፈው አስር ጊዜ እየመለሰ ወደ ኪሱ ይከታል፡፡



ውሮም ሌላ የሸቦ መኪና ይዞ በአጃቢነት ተሰልፏል፡፡ ቀጢሳው በከረሜላ ወረቀት የጠቀለለውን ጠጠር ለከበቡን ታዳ ሚዎች በተነላቸው፡፡ ጭብጨባው ጦፈ፣ ዘፈኑም ደመቀ፣ እልል ታው ቀለጠ፡፡ በደንቡ መሠረት የኃይሉ ዶሮን ሹራብ ይዤ ከኋላ ተሳፈርኩ፡፡ ከጎኔ እጇን ከእጄ ያቆላለፈችው መቅደስ ተሳፍ ራለች፡፡

ሚዜዎቻችን በውሮ መኪና ተሳፈሩ፡፡ መስፍን ፑሉቶ እንደ የተሸነቆረ ጣሳ እንደ ካሜራ ዓይኑ ላይ እየደገነ "ገለል በሉ!" እያለ ሙሽሮቹን በተለያየ አቅጣጫ ፎቶ ያነሳናል፡፡

በአጠገባችን ለጉዳያቸው የሚያልፉና የሚያገድሙ ትላልቅ ሰዎች ጭልጥ አድርጎ ከወሰዳቸው ሃሳብ ባነው ለደቂቃም ቢሆን ወደ ገሃዱ ዓለም በመመለስ "ምን ተገኘ?" ብለው ይጠይቃሉ፡፡ አንድም ቀን ሲሰቁ ዓይቻቸው የማላውቀው አባባ ጥላሁን እንኳ ፈገግ ብለው "ያሳድጋችሁ! ለወግ ለማዕረግ ያብቃችሁ" ሲሉ ሰማኋቸው፡፡

እማዬ ወደ ገበያ ስትሄድ "እነማን ናቸው ሙሽሮቹ?" ብላ ጠየቀች፡፡ እኔ መሆኔን እንዳየች" ውይ የእኔው ቶንጋዬ ነው እንዴ ሙሽራው? ቱ! ቱ! ከዓይን ያውጣችሁ"ብላ መርቃን፣ "ታዲያ ወዴት ነው የምትሄዱት?!"

ሲሳይ ጎቢጥ "ሽርሽር!" አለና መለሰላት፡፡

"እንዳትርቁ"! ብላ ፈገግ ብላ አስተዋለችን፡፡

በኃይሉ ዶሮ ሾፌርነት ወደፊት ተጓዝን፡፡ እየተጨፈረ ጉዞው እስከ አበራ ወፍጮ ቤት ቀጠለና መኪናውን ተጠምዞ ወደነበርንበት ቦታ መለስን፡፡

ጨዋታው እንደቀጠለ ነው፡፡ ለምሳ የስንስል ቅጠል ቀርቦ ልን፤ በቆርኪ መጠጥ ታደለን፡፡ ደስ እያለን ተበላና ተጠጣ፡፡ እንደገና ዘፈን ተጀመረ፡፡ ሚዜዎቻችን ተነስተው እስክስታውን አስነኩት፡፡

በዚህ መካከል የመቅደስ ታላቅ እህት ልጃገረዷ መዓዛ መጣችና "በቃ ደከሚቸዋል፡፡ አሁን ትንሽ መተኛት አለባቸው" አለች፡፡

ሙሽሮቹ እየተጨፈረልን ከበረንዳው ላይ ተነስተን እነ መቅደስ ቤት ገባን፡፡ መዓዛ አመቻችታልን ታጣፊ አልጋዋ ላይ ጋደም አልን፡፡ ይህን ጊዜ የመቅደስ እናት የእማማ ማሚቴ ድምፅ ከውጪ ተሰማ፡፡ መአዛ እየሳቀች ከቤቱ ውስጥ ወጣች፡፡ እማማ ማሚቴ መቅደስ ከንዴን ተንተርሳ ጋደም እንዳለች አዩን፡፡ ከው ብለው ቀሩ፡፡ ዘንቢላቸውን በቁማቸው ለቀቁት፡፡ እሳት ለብሰው እሳት ጎርሰው"አንተ ቆሮቆንዳ ቶንጋ! ለመሆኑ ምን አስበህ ነው ልጄን አቅፈህ የተጋደምከው? አንተ ምናምንቴ!" ብለው ቁንጮዬን ጨምድደው ሸቀብ ሳቡኝ፡፡ እንደ ድመት እየጮህኩ ተንጠለጠልኩ፡፡ "መልሰልኝ እንጂ! ገና እንብርትህ ሳይደርቅ!? ምን ልታረጋት ነበር?!" ብለው መዳብ ቀለበት

ጉዳይ ላይ ይወያያሉ። በሽምጋይ አማካኝነት የችግሩን ምንጭ ይመረምራሉ። ይቅር ለእግዜር ተባብለው፣ እንደ ጥንቱ ተዋደውና ተፋቅረው መኖር ይጀምራሉ። እኔንም የዚያኔ "ደግ አደረጉ! ቢመቱህም እናትህ ናቸው!" እማዬ ትበለኝ እንጂ፣ ችግሩን በበነጋው እንደሚመረምሩት ገምቻለሁ።

ያ ጣፋጭና መራራ ትዝታዬ ግማሽ ምዕተ ዓመት ሊሞላው ጥቂት ዓመት ነው የቀረው። ይሁን እንጂ የባልና ሚስት ጨዋታ ትናንት የተከናወነ ያህል አሁንም ጎልቶ እንዲታየኝ የእማማ ማሚቴ የመዳብ ቀለበት ማንተሙን አናቴ ላይ አኑሯል።

## ከሀሁ እስከ ወንጌል

*"ልጅነቴ እንደ ግነት ተውኔት (ሜሎድራማ) ነበር። እየተሰደቡ 'እየተገረፉ' መማር መቼም ለእኔ ሜሎ ድራማ ነው"*
*ዤራር ደፓርድየፖ (ፈረንሣዊ የሲኒማ ተዋናይ)*

እነሆ ትምህርት ቤት ገብቼ እንደገና የመማሬ ጉዳይ የግድ ሆነ። ግዴታውን የፈጠረውም እኔ በተከታታይ ሰሞን የሠራኋቸው መጥፎ ተግባሮችና ያጋጠሙኝ አደጋዎች ነበሩ። አንደኛው በመዓዛ ገፋፊነት ከመቅደስ ጋር 'ባለጌ ሥራ' ለመሥራት መስማማቴ ሲሆን፤ ሌላው ከኃይሉ ዶሮ ጋር ተጣልተን ፊታችንን በኃይል ተሞነጫጨርን። እንዲሁም የተሰጣ እህል ሳጠብቅ 'እሽሽ አትበሉኝ የሹም ዶሮ ነኝ' ያለው የአናጢው የአባባ መሹ ዶሮ ከንፈሬን በመንከሱ የደረሰብኝ የመቁሰል አደጋና ሌሎች ችግሮች ተደራርበው ቄስ ትምህርት ቤት የመግባቴን ጉዳይ አፋጠነው።

ወላጆቼ በትንሽ በትልቁ ጉዳይ መደናገጡ ተደራርቦባቸዋል። በየቀኑ ከሚከሰት ነፍስን ከሥጋ የሚለይ ችግር ለመገላገል እኔን ቄስ ትምህርት ቤት ማስገባት መፍትሔ እንደሆነ ወላጆቼ ከጎረቤቶቻችን ጋር መክረዋል። እኔም ጥፋቴን ስለተቀበልኩ ቄስ ትምህርት ቤት መግባቴ ጥሩ እንደሚሆን ገመትኩ። ዝግጅቴ እንደቀድሞው በፍጥነት ተከናወነ። በቅዱስ ቂርቆስ ቤተክርስቲያን ውስጥ በሚገኘው ቄስ ትምህርት ቤት ሊያስመዘግበኝ ይዞኝ የሄደው አሁንም አባቴ ነበር።

ይህንን የሕይወቴን ምዕራፍ ለመቃኘት በቅርቡ ወደ ለማዕቱ ቅዱስ ቂርቆስ ቤተክርስቲያን ዘልቄ ነበር። ቤተ



ክርስቲያኑ በአሁኑ ጊዜ ታድሷል። ምዕመናን ፀሎት የሚያደርሱበት ቦታ በጥሩ ሁኔታ ተገንብቷል። ቤተመቅደሱ ከሙታን አምባ በግንብ አጥር ተለይቷል። ድሮ ችግኝ የነበሩት ተክሎች ዛሬ ዕድሜ የጠገቡ ዛፎች ሆነዋል።

በልጅነቴ አንድ ተማሪ ፊደል እየቆጠረ የቀብር ሥነ ሥርዓት ሲፈጸም ያስተውላል። ጉልት የሚገበዩ ሰዎች በቅርብ ርቀት ይታያሉ፤ ጫጫታቸውም ይሰማል። አቃቢቶች ከመቃብር ቤታቸው ወጥተው ፍርፋሪያቸውን ካቡ ላይ ሲያሰጡ ይስተዋላሉ።

ፊደል የምንቆጥረው በደወል ቤቱ ውስጥ ሲሆን፤ ፀሐይ ሙሉ ለሙሉ ወጥታ መለብለብ ስትጀምር በርጩማችንን ይዘን ጥላ ወዳጠላበት አቅጣጫ እንድንዞር የኔታ ያዙናል። ለየኔታችን ፀሐይ ሰዓታቸውም ጭምር ነበረች። ለዕረፍት የሚለቁንም ሆነ፣ ለምሳ ወደየቤታችን የምንሄደው በፀሐይ ጥላ አለካካቸው ነበር። በሃሳብ ሲመስጡ ወይም ሲቆዝሙ አለቃችን ያስታውሳቸዋል።

የፊደል ዘር ለመለየት በምንጣጣርበት ወቅት ትኩረታችንን የሚስቡ በርካታ ጉዳዮች ይከሰታሉ። ለቀብር ወደ ቤተ ክርስቲያኑ የሚገቡ ለቀስተኞች ሲጯጯሁ ትምህርታችንን አቋመን አለቃቀሳቸውን እናስተውል ነበር። ወይም አንዲት ለዕለት ውሎዋ የምትሯሯጥ አይጥ ከካቡ ስር ትጠጣና አፍጣ ታየናለች። አንዱ ሕፃን እንዳየት "አይጥ!" ብሎ ይጮኻል። ወደ አፈጠጠበት አቅጣጫ እናያለን። ቀልባችን ሁሉ ዓይጧ ላይ አርፎ ፀጥ እንላለን። በማንጎላጀት ላይ የነበሩት የኔታም ጫጫታው ጋብ ሲል ይነቃሉ። "ተማሩ!" ብለው አለንጋቸውን ሲሰነዝሩ ጫፉ ያረፈበት ልጅ የተመታ አካሉን እያሻሸ ማልቀስ ሲጀምር እንደገና መንጫጫታችንን እንቀጥላለን።

ብዙም ሳልሰነባብት ሀሁን አጠናቅቄ ሀ- ግእዝ ሁ -ካእብ መማር ጀመርኩ። ይሁን እንጂ በዘመኑ ትምህርቱን የምንማርበት ስልት በልጅ አቅም የሚሸከሙት ባለመሆኑ ታከተኝ። ልጅን አባብሎና አግባብቶ በጨዋታ መልክ የሚገበይ ትምህርት ባለመሆኑ ጠላሁት። ልክ ወላጆቻችን በዚያው በልጅነት ጊዜ ጭንቻቸው ላይ አስቀምጠውን አፍንጫችንን ስንነው አብሽ፣ ወይም ወተት አልያም መድኃኒት እንደሚግቱን ሁሉ፣ ሁሉም ነገር የሚካሄደው በግድ በመጋት ነበር። በዚህ ወቅት ምንም የልጅን ፍላጎት በመከተል የሚካሄድ ነገር አልነበረም። በዚህ ምክንያት ከአባቴ ጋር ነጋ ጠባ መጨቃጨቅ ጀመርን። እናቴ መማሩ እንደሚጠቅመኝ ለማሳመን ትውተውተኛለች። ዕድሜ ልኬን እንዲያሸንፈኝ የተፈጠረው አባቴ ግን በኃይል ያስገድደኛል። ይሁን እንጂ የእናቴ ፍቅርም ሆነ የአባቴ ኃይል ትምህርቴን እንድወድ አላደረጉኝም። 'ፈረስን ወደ ወንዝ መውሰድ ይቻላል፤ ውሃ እንዲ ጠጣ ማድረግ ግን አይቻልም' እንዲሉ፤ የተለያዩ ሰበብ አስባቦችን እየፈጠርኩ ከትምህርት ቤት እቀራለሁ። ቅዳሜና

ፍባቸው ልምጮች ቢጠራቀሙ ኖሮ አንድ ምባድ አስምተው
ቡሃቃ ሙሉ ሊጥ ያስጋግሩ ነበር ብዬ እገምታለሁ::
የኔታም ያረፈደውን ቀጥተው "ተማሩ" ሲሉ ያዙናል:: ሀሁ
የሚማረው ከሚያስተምረው ጋር ተጣምሮ ይቀጥራል:: ሀ -ግእዝ
ሁ -ካኢብ...፣ አቦጊዳ፣ መልዕክተ፣ ወንጌልና ዳዊት በየብጤው
በመሆን ፊደላቱን መቁጠር ይያያዛል::
በቄስ ትምህርት ቤት ሕይወቴ እኔና አብሮ አደጎቼን የሚ
ያስደስተን ቀን እምዬ ማርያም በ21 የምትነግሥበት ዕለት ነበር::
በዓሉ እንደነገ ሊሆን በዋዜማው "ልጆች ነገ የእመቤታችን ንግሷ
ነው:: ስለዚህ ትምህርታችሁን እንድትገልጽላችሁ፣ ፀበል ፀዲቋን
እናደርሳለን" ሲሉ የኔታ በሚቀጥለው ጠዋት አራት ፍራንክ ከወላ
ጆቻችን ተቀብለን እንድንመጣ ይነግሩናል:: የሁላችንም ቤተሰ
ቦች ያለምንም ጥያቄ ይሰጡናል::
በ21 ጠዋት ማንም ሳይቀሰቅሰኝ እነቃለሁ:: አራት ፍራ
ንኳን ከአባቴ ወይም ከእናቴ ተቀብዬ ጭብጥ አድርጌ እይ
ዛታለሁ:: እጄ ውስጥ ማንቲሟ ያልባታል:: ከሰፈሬ ልጆች ጋር
ተጠራርተን ወደ ትምህርት ቤት እንሄዳለን:: ቤታቸው ቅርብ
የሆን ልጆች የሻይ ማንቆርቆሪያ እና ሣህን ያመጣሉ:: ገበያው
እዚያው በመሆኑ የሚፈለገው በፍጥነት ይሸመታል:: ሻዩ ይፈ
ላል፣ ዳቦው ይባረክና እንቋደሳለን:: በዚህ ዕለት እጅ በጆሮ
የለም፣ መንበርከክ የለም፣ እጅህን ዘርጋ የለም፣ ቂጥህን እዙር
የለም:: በአጠቃላይ ግርፊያ የለም:: በነፃነት ስንጨዋወት ውለን
በጊዜ ወደ ቤታችን እንመለሳለን::
ሌሎቹ አስደናቂና አስደሳች ዕለታት ደግሞ በፍልሰታ ፆም
ሰሞን ይመጣሉ:: እኔ አስራ ለድስቷንም ቀን እቀርብ ነበር::
በዚያን ሰሞን የየኔታ አለንጋም ሆነ የቤተሰብ ቁጣ ይቀራል::
አንድ ነገር አጥፍቼ አባቴ ቢቆጣ እንኳ "ተወው! ቆርቧል" ስትል
እናቴ ትከለክለዋለች:: እሱም የቃጣውን እጅ ሰብስቦ ያደ
ርጋል::
ረስቼው ቁርሴን የበላሁ ዕለትም ቢሆን እቀርባለሁ:: የኔታ
አራት ሰዓት ላይ የምንቆርበውን እንድንሄድ ሲፈቅዱልን "ቁር
ሳችሁን በልታችሁ የምትቆርቡ ካላችሁ ትቀሰፋላችሁ" ሲሉ እየሰ
ማሁ ለቁርባን እወጣለሁ::
ከዚህ መለስተኛ እስር ቤት ማምለጫ ስለሚሆነኝ በጣም
ብፈራና ብጠራጠርም ቆርቤ መቀሰፉን ትንሿ ሕሊናዬ የመረ
ጠችው ይመስለኛል:: ይሁን እንጂ ቤተ መቅደስ ውስጥ ከጓደኞቼ
ጋር ተሰልፌ ሥጋ ወደሙን ልቀበል ስል ልቤ መሸበር ይጀ
ምራል:: "እግዚአብሔርዬ እባክህን አትግደለኝ!" እያልኩ በሆዴ
ቀሳውስቱ በአፌ የሚሰጡኝን ተሰጥኦ እቀበላለሁ::
ወደቤት ስሄድ አፌን ሸፍኜ፣ ከልጆች ጋር ሳልላፋና አር
ጥበት ሳይነካኝ እውላለሁ:: የምጫወተውም በእርጋታ ነበር::



ጀምበር እንደ ጠለቀች ቤት ገብቼ ራቴን በልቼ እግሬን ሳልታ
ጠብ ባገኘሁት ቡትቶ ጠረግ ጠረግ አደርግና እተኛለሁ:: በቆረ
ብኩ ማግሥት ድብን ካለ እንቅልፍ ላይ ነቅቼ ራሴን በሕይወት
ሳገኘው እግዚአብሔር እንደማረኝ አምናለሁ:: "ዛሬም እቆር
ባለሁ!"
"እሽ እንዳልክ!"
"ቁርሴን ስጪኝ::"
"እንደሱማ ነውር ነው ትቀሰፋለህ!"
"ትናንትና የኔታም እንደ አንቺ ብለውኝ ነበር:: እኔ ግን
አለሁ!" ስላት እናቴ በኃይል ትስቃለች:: በሳቅዋ መካከል መረታ
ትዋን እመለከታለሁ:: ወደ ጓዳ ይዛኝ ገብታ ቁርሴን ትሰጠኛ
ለች:: "ልጆች ገብተው እንዳያዩኝ ጠብቂልኝ" ስልም ዘብ እንድ
ትቆምልኝ አዛታለሁ:: ተመግቤ እንዳጠናቀቅኩ፡
"አንተስ ማንም አይችልህ የምትገርም ፍጥረት!" እያለች
ነጠላ አጣጥፋ ታከናንበኛለች:: ያለምንም ሸኚ ከአብሮ አደጎቼ
ጋር ወደ ትምህርት ቤት እንሄዳለን::
አስደሳችና ተወዳጅ ዕለታት ምንጊዜም ቢሆን አጭር
ናቸው፣ ቶሎ ያልፋሉ:: እንደገና ከፊደል ጋር ትንቅንቅ እንጀ
ምራለን:: ጠዋት ወደ ትምህርት ቤት መሄድ የሚቀፈኝን ያህል
ማታ ወደ ቤቴ መመለስ ያስደስተኝ ነበር:: ልክ የምንለቀቅበት
ደወል ሲደወል ከጓደኞቼ ሁሉ ቀድሜ ከቤተክርስቲያን ግቢ
በሩጫ እወጣና "አንደኛ!" ማለት ያስደስተኛል:: ይሁን እንጂ
አንዳንድ ቀን በርጬማዬን ወይም ጠርሙሴን ረስቼ ወደ ቤት
እመለስ ነበር::
የዕለቱ ትምህርት ሁልጊዜ የሚጠናቀቀው ሕይወቴን በሙሉ
በሕሊናዬ ተቀርፆ በቀረው "አባታችን ሆይ!" ፀሎት ነበር::
ከዚያም በወር አንዴ የምታሳርፈንን እመቤታችን ድንግል
ማርያምን ተማፅነን፣ ማሳረጊያችን "በሰይጣን ጉሮሮ አጥንት ይቀ
ርቀር፣ በየኔታ ጉሮሮ ጠጅ ይንቆርቆር" ብለን ሩጫችንን እና
ስነካዋለን::
በእንዲህ አይነት ስሜት ውስጥ እያለሁ ከአባቴ ጋር
መንገድ ላይ ከተገናኘን "ምነው ጠዋትም እንዲህ እየሳቅህ ስትሄድ
ባይህ!" ይልና ሊያግዘኝ በርጬማዬን ወይም ጠርሙሴን ይቀበ
ለኛል:: ሣቄ ተጋብቶበትም አብሮኝ እየሳቀ በፍቅር እጅ ለእጅ
ተያይዘን ወደ ቤታችን እንሄዳለን::
አብረውኝ ቄስ ትምህርት ቤት የተማሩትን ልጆች ጥቂቶ
ቹን እስታውሳለሁ:: ጃምቦና ሲራክ ቁንጮ ደግሞ በተለየ ገጠመ
ኛቸው ምን ጊዜም አልረሳቸውም::
ጃምቦ ከስቶኪንግ የተሠራ ትልቅ የጨርቅ ኳስ ነበረው::
ሁሌም በእረፍት ሰዓት ምትሮሽ ስንጫወት እሱ በረኛ ሆኖ እኔ
እለጋለሁ:: የእሱ የበረኛነት ፍቅር ተጋብቶብኝ እኔም በቅጡ
እለማመድ ነበር:: ቤታቸው ከትምህርት ቤታችን አጠገብ ስለነበር

እያልኩ ለአንተ ሳስረዳ እዚሁ ተገሽሬልህ ልደር?!» እጄን ሳብ አድርጋ ቁልቁል መራመድ ጀመረች::

በዚያ ትርምስ አንድም ቃል ሳትተነፍስ በሕዝቡ መካከል እየተሽለኮለክን አለፍን:: ዳቦዬን ጨረስኩ:: ውሃ ጠማኝ:: በምንሄድበት መንገድ አንዱ ግቢ ውስጥ የቧንቧ ውሃ ድምፅ ሿ ሲል ሰማሁ::

"ውሃ ልጠጣ?!" አልኳትና ከእጇ አምልጬ አጠገባችን ባለው ግቢ ዘው ብዬ ገባሁ:: "ምን አይነት ቢራቢሮ ፍጥረት ነው?..." እያለች ተከተለችኝ:: ከቧንቧው አጠገብ ውሃ ሲቀዳ ያገኘሁት እኩያዬ የሚሆን ልጅ በመሆኑ ውሃ እንዲያጠጣኝ ጠየኩት:: እሷም ደርሳብኝ ለመነችልኝ:: ልጁ በጣሳ ከባልዲው ጠልቆ ሰጠኝ:: ጠጥቼ እንደጨረስኩ እጄን ጥብቅ አድርጋ ይዛኝ ተመልሰን ወደ መንገዱ ወጣን::

ከፊት ለፊታችን ባለው ትልቁ ግቢ በር ግራና ቀኝ ላይ ቀጥ ብለው የቆሙትን የክቡር ዘበኛ ወታደሮች አየሁና "ይሄ የማን ቤት ነው?"

"የአባባ ጃንሆይ ቤት ነው:: ታላቁ ቤተ መንግሥት ይባላል::"

"ውይ! የአባባ ጃንሆይ ቤት ነው? በናትሽ! በናትሽ! ሄደን እንጨብጣቸው?!"

ከትከት ብላ ሳቀች:: 'የደላው ሙቅ ያኝካል' ጃንሆይ እንዳንተ ሥራ ፈት መሰሉህ? በል ልጄ እኔ እንዳንተ አልደላኝም:: ፈጠን ፈጠን ብለህ ተራመድ:: ለመሆኑ ምን ልታደርግ ከቂርቆስ እዚህ ድረስ መጣህ?"

"ውይ! ግን ተይው!!"

"ለምን?"

ቅንድቤን በጣቴ ጠቆምኳት::

"ቅንድብህ ምን ሆነ?"

"እ! አማላቅ መሰለሽ? እማማ ረታሽ ነግረውኛል 'ኮ::"

"ምን ነገሩህ እማማ ረታሽ?"

"ጃንሆይ ካገኙኝ ለቀሪጥ..."

ሳቅዋን መቆጣጠር አልቻለችም:: "እንደው ለመሆኑ ምን ልታደርግ ነው ከዚያ እዚህ ድረስ የመጣኸው?" አለችና በአደፈ ነጠላዋ ዕንባ ያቀረሩ ዓይኖችዋን አባበሰች::

ምንም ሳልፈራት ስለ አጠፋፌ እውነተኛውን ምክንያት ነገርኳትና "እኔ'ኮ ሙዚቀኞቹ ከተማዋን ዞረው ተመልሰው እተነሱበት ቦታ ላይ ሲበታተኑ ሰፈሬ መመለስ አያቅተኝም ብዬ ነው:: ሲሳይ ኀቢጥን ግን ሳገኘው አለቀውም::"

"ማነው ደሞ ሲሳይ ኀቢጥ? እቤት ስትገባ አባትህ ትንሽ ሳያቀምሱህ አይቀሩም::"



"ኀቢጥ ካቃጠረ እገረፋለሁ፤ ካላቃጠረ ግን ማንም ስላላየኝ አልገረፍም::"

"በል ዝም በል!" አለችኝና በራሷ ሃሳብ ጭልጥ አለች:: አረማመዷ ፈጣን ባለመሆኑ ለጉዞዬ ብዙም አላስቸገረኝም:: ውሃ በብዛት ስለጠጣሁ ሆዴ ውስጥ ሲንቦጫቦጭ ይሰማኛል:: መኪናዎቹ በአጠገባችን ሽው እያሉ ሲያልፉ አንዲት ሃሳብ መጣችልኝ:: በመኪና የመጓዝ ልምዴን ላካፍላት ፈለኩ:: "አባቴ መርካቶ ለባለ ሲሼንቶ ስሙኒ ከፍሎ ጭኑ ላይ አስቀምጦኝ ብዙ ጊዜ ወስዶኛል:: ታዲያ ሲሼንቶ ውስጥ ሆኜ ሰው ሁሉ ወደ ኋላው ነው የሚሔደው:: አሁን እኮ መኪናው በአጠገባችን ሲያልፍ እኛ ወደኋላ እየሮጥን ነው መኪና ውስጥ ላሉት ሰዎች የምንታያቸው::"

ከትከት ብላ ሳቀች:: ነጠላዋን ተከናንባ በሳቅ በሚያበሩ ዓይኖቿ እያየችኝ "አንተ እዚህ ትፈላሰፋለህ:: እናትህ ግን ይሄኔ..." አለችና በረጅሙ ተንፍሳ ጉዞዋን ቀጠለች::

እኔ ግን ወሬዬን ቀጠልኩ:: "ደግሞ 'ኮ ሰው ብቻ መሰለሽ ወደኋላ እሚሄደው? ሜዳውም፣ ቤቱም፣ ዛፉም፣..." ስል አንድ ውሻ ባጠገቤ አለፈ:: "ውሻውም ጭምር ነው" ስላት ዳግመኛ ሳቋ አሸነፋት::

"አንተ ኀል ጥርስ! አፍህን ዝጋ" አለችኝ::

"ጥርሴ'ኮ ተሰብሮ አይደለም!"

"ታዲያ ምን ሆነህ ነው?" ጨዋታዬን ወዳዋለች::

"ሰባት ዓመት ስለሞላኝ ነው የተነቀለው::"

"እንዴት ተነቀለ?"

"በጣም ሲነቃነቅ እማዬ በክር ካሰረችው በኋላ፣ አባበለችኝ አባበለችኝና ሳብ አደረገችው" አልኩና፣ ጥርሴን እንደ ምነቅል ሁሉ ስወራጭ እጄ ከእጇ አፈተለከ:: መልሳ አልያዘችኝም::

"የተነቀለውን ጥርስህን የት አደረከው?"

እኩል እየተራመድን አንጋጥጬ አሳየኋትና "ለወፊቱ ሰጠኋት:: የርሷን እንድትሰጠኝ" አልኩና በመዝሙር፣

*ወፌ! ወፌ! የኔን ጥርስ ላንቺ!*

*የንቺን ጥርስ ለኔ* ብዬ ጣራ ላይ ወረወርኩት አሁን ይበቅልልኛል::"

"መቼ ነው የተነቀለው?"

"ድሮ! እንዲበቅልልኝ ጠዋት ጠዋት በአመድ እየታሸልኝ ነው::"

"ወሬኛ ቢጤ ነህ፤ ስምህ ማነው?"

"ተስፋዬ ዜራሞ::"

"ዜራሞ ደግሞ የምን ስም ነው?"

"የአባቴ::"

"እናትህስ ማን ይባላሉ?"

"ባሎቴ ጋጋ"

"እንዴ'! አንተ አውቅሃለሁ:: ስምህ ፋንጌ አይደለም?"

"ተቀይሯል! አሁን እኮ አንደኛ ክፍል ነኝ"

"እናትህ ጉልት እንጀራ ይሸጣሉ አይደል?!"

"አዎን::"

"ከቦኖ ውሃው አጠገብ አይደለም መደባቸው?"

"አዎን:: ከርሷ አጠገብ እማማ ብርሌ ናቸው እሚቀመጡት:: ከዚያ በኋላ እማማ ሸቃሽ..."

"ዝም በል! ተዋውቀናል" አንተ ዙረታም ቆይ ዋጋህን ታገኛታለህ" አለችኝና ሳቅ ጨዋታውን አቁመን በፍጥነት መራመድ ጀመርን::

መናፈሻው አካባቢ ስንደርስ በራሷ ሃሳብ ተመስጣ ቆመች:: መንገድ የጠፋት መሰለኝና ልረዳት ፈለኩ:: "መንገዱ ጠፋብሽ እንዴ? ቆይ በአንዴ አሳይሻለሁ" አልኩና ምራቄን ግራ እጄ ላይ ተፋሁ:: በቀኝ እጄ ምራቄን በካራቴ ስመታ፣ ምራቁ አብዛኛው ወደ መናፈሻው ተረጨ፤ ወዲያው ወደላይ ቀና ብዬ አየኋትና "በዚህጋ እንሂድ::"

በሙዚቃዊ ሳቅዋ አስተጋባ:: በዚያው ሻካራ እጅዋ ክንዴን ይዛኝ "በእንዲህ አይነት ጨዋታ መንገድ ይፈለጋል? የጠፋ ዕቃ ነው እንጂ::"

"እረ? መንገድም ይፈለጋል!" አልኳትና አንዱን የወደቀ ቆርኪ በእግሬ በሰኞ ማክሰኞ ጨዋታ ስልት መታሁት::

"በምራቅ መንገድ ማወቅ ከቻልክ ለምን ቅድም ከስድስት ኪሎ ወደ ቂርቆስ ለመመለስ አልተጠቀምክበትም?"

"ቅድም እኮ ደንግጬ ነበር:: ባልደነግጥ ኖሮ በምራቄ ምልክት እሄድ እሄድና ሰፈሬ ግብት እላለሁ!" በፈጣን ድምፅ ነቃ ብዬ መለስኩላት:: በራስ መተማመኔ እየጨመረ ነበር::

በፈገግታ እያየችኝ "መልስ አታጣም መቾስ" አለቺኝ:: በምራቄ አቅጣጫ መሪነት በጠቆምኳት መንገድ ቁልቁል ይዛኝ ተጓዘች:: ሁለት የክቡር ዘበኛ ወታደሮች ግራና ቀኝ ጠብመንጃዎቻቸውን ይዘው ቀጥ ብለው የቆሙበት በር ላይ ደረስን:: «ይኼም የአባባ ጃንሆይ ቤት ነው?» ጠየኳት መሪዬን::

«አንተ ቆቅ ነህ!» ኢዮቤልዩ ቤተመንግሥትን ታውቀዋለህ?» ጠየቀችኝ::

«እዎን!» አልኳት፤ ግን ውሸቴን ነው::

የአዋቂነት መንፈስ በሠራ አካላቴ ናኘ:: እስጢፋኖስ አካባቢ ደረስን::

"ከዚህ በኋላ ባቡር መንገዱን ከተሻገርኩኝ ሰፈሬ መድረስ እችላለሁ"

"አሁንማ ቤትህ ካላደረስኩህ አልመለስም ሆ! የትዬ ባሎቴ ውስታ!" አለች ግማሽ ለራሷ እያጉተመተመች::



"እረ! መጥፋቴን ነግረሽ ልታስገርፊኝ" ብዬ ማልቀስ ጀመርኩ::

"ዝም በል! አሁን እኔ ባላደርስህ ሊቀርልህ ኖሯል? አታይም፣ መሽቷል እኮ!" ማልቀስ መጀመሬን አይታ "በቃ አትነፋረቅብኝ መሿለኪያን እንዳሳለፍኩህ ብቻህን ትሄዳለህ::"

እንዳለችውም መሿለኪያን እንዳለፍን ቆማ እያየችኝ እኔ በልጅ እግር በሶምሶማ ሩጫ ወደ ሠፈሬ ሄድኩ:: ጨልሟል ግን ጨረቃ ሙሉ ብርሃንዋን ፈንጥቃለች:: ትከተለኛለች:: ስሮጥም ከጎን ከጎኔ እያበራችልኝ ሠፈር ደረስኩ:: ጨረቃ ሁሌም ማታ ማታ እኔን መከተል ትወዳለች::

ሦስት ልጆች በዕለቱ ጠፍተን፣ የተገኘው ሲሳይ ኀቢጥ ብቻ ነው:: ኃይሉ ዶሮ የደረሰበት አይታወቅም::

ቀጢሳው የኔን መምጣት በርቀት ሲያይ ለቤተሰቦቼ ለመናገር ወደእኛ ቤት ሮጠ:: መኩዬ ቀጫጫው በፍጥነት እኔ'ጋ መጥታ ስለ ሠፈራችን የዕለት ሁኔታ መረጃ ሰጥታኝ የት እንዳመሸሁ ጠየቀችኝ:: መልስ ሳልሰጣት ከእኛ ቤት ጎረቤቱ ሁሉ ተግተልትሎ ወጣ:: አባቴ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ ሊፈጀኝ ሲል፣ አባባ አጋፋሪ በከዘራቸው ሳብ አድርገው አበረዱት::

ወደኔ ዞረው "ፋንጋይ፣ የት ውስህ መጣህ?" አሉኝ በለዘብታ::

እውነቱን ነገርኳቸው::

"ኃይሉንስ አይተኸዋል?" ሲሉኝ የዶሮ እናት እማማ ሸጊቱ የሰማይ ስባሪ እሚያክል ቂመናቸውን እያንዠበበቡብኝ በዕንባ የደፈረሰ ዓይናቸውን እያቁለጨለጩ መልሴን ይጠብቃሉ::

"ኃይሉ እኮ ከእኔ ጋር አልሄደም!" አልኩ::

እማማ ሸጊቱ "ወይኔ ልጄን! ይሄኔ ዓይኑን አውጥተው መለመኛ አድርገውታል! ወይኔ! ወይኔ" ሲሉ ኡኡታቸውን አቀለጡት:: ማታ የዶሮ ወጥ እየሠራሁ ካልበላሁ አልተኛም ብሎ ሌሊቱን ቁጭ ብሎ አጋመሰ:: እሷንም ሳይቀምስ እንቅልፍ አሸነፈው! ወይኔ ልጄ! እንደዚያ እንዳማረው ድፍት ብሎ ይሆናል! ኡ! ኡ!"

"ጠዋት አብራችሁ አልነበራችሁም?" አባባ አጋፋሪ ደግመው ጠየቁኝ::

"ጠዋትማ አብረን ነበርን፥: እኔና ሲሳይ ጠፍተን ስንሄድ ቀጢሳው ኩኩሉ እያለ ነበር:: እኔና ሲሳይ የምንደበቅ መስለን ስንጠፋ ኃይሉ ወደ ግቢያቸው ገባ:: እርሱ'ኮ ኩኩሉ ስንጫወት ብዙ ጊዜ እሚደበቀው እቴነሽ አልጋ ስር ነው፤ እዚያ አይታችሁታል?"

ታላቅ እህቱ እቴነሽ በሩጫ ወደ ቤታቸው በረረች:: ጎረቤቱም ተከተላት:: እኛ እነኃይሉ ግቢ በር ላይ ስንደርስ እቴነሽ እየሳቀች ወጥታ "አልጋ ስር ተኝቷል!" ብላ አበሰረችን::

በኃይሉ ዶሮ ባልተጠበቀው መንገድ መገኘት ነገሩ ሁሉ ወደሳቅ ተለወጠ:: የኔ ጥፋተኝነትም በዚያው ተረሳች::

## ቤት ለእንግዳ

*"ተረት ተረት"*
*"የላም በረት?"*
*"ሆድህ ይተርተር በብረት"*
*እማዬ!*

በቤታችን ውስጥ አልፎ አልፎ እንግዳ ይበዛል:: አንዳንዴም የተማከሩ ይመስል የአባቴና የእናቴ ዘመዶች ከየጠቅላይ ግዛቱ ይመጣሉ::እንግዳ ሲመጣ ደግሞ አባቴና እናቴ ቤት ያፈራውን ለማቀራረብ ጉድ ጉድ ይላሉ:: የእንግዶቹ መምጣት ደስታንም ኀዘንንም የሚያስከትል ሲሆን፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ለዘመናት የማይረሳ ትዝታ ትተው የሚሄዱ ናቸው::

በአንድ የበጋው ወር መገባደጃ ላይ ሳርያን ኮትና ተፈሪ ቅድ ሱሪ የለበሰና ቦት ጫማ ያደረገ ባላገር ቤታችን መጣ:: ለአባቴ የሩቅ ዘመዱ ነበር:: ዛሬ በምናቤ ስስለው እጭር፣ በጋያ ጢስ የበለዙ ጥርሶች፣ የደፈረሱ ዓይኖችና የተሸበሸበ ግንባር ያለው የቀይ ዳማ ነው:: እነዚያ ድፍርስ ዓይኖቹ ደግሞ ንቁዎችና ሁሉንም ነገር በጥንቃቄ የሚያስተውሉ ናቸው:: ከፍተኛ የትምባሆ ሱስ ስላለበት በላይ በላዩ ግስላ ሲጋራውን ያጤሳል:: ሲጋራውን ገንዘብ ከኪሱ አውጥቶ አይገዛም:: ቤተ ዘመዱ ይሸምትለታል፤ አንድ ቀን የሚገዛበት ፍራንክ ቢያጣ እማዬ እንድ ትሸምትለት ጠየቃት::

እማዬም ፈገግ ብላ "ምነው ቅድም ቱማ ውሃ ጠጣበት ብሎ አንድ ብር አልሰጠህም?!" አለችና ጥያቄውን በጥያቄ መሰስችለት::

በምፀት ሳቀና "ብር ተመንዝሮ ሲጃራ ይገዛል? ብር ግብር ይከፈላል እንጂ!"

እማዬ የኮረኮሯትን ያህል ሳቀች:: ሰውዬውም በእናቴ የብር ውሎን አለማወቅ ሳቀባት:: ይህን አስቂኝ አጋጣሚ አባቴ ከገበያ እንደተመለሰ አጫወተችው:: አባቴም ስቆ አንድ ፓኬት ግስላ በስድሳት ፍራንክ ገዛለት:: በቤተሰባችን አስደናቂ አጋጣሚ በተነሳ ቁጥር ይህ ገጠመኝ ለዛው ሳይነጥፍ ሁሌ እንደ አዲስ ያስቃቸዋል::



ከዓመታት በኋላ ፍቅር እስከ መቃብር ውስጥ "ባላገር የሚበላው ቢያጣ የሚገብረው አያጣም" የምትለዋን አባባል ሳነብ ተራዬን እኔም ሳቅሁ::

እንግዳን መቀበልና መሸኘቱን ወላጆቼ ቢወዱትም እኔ ግን ደስ አይለኝም:: በእንዲህ አይነት ዕለት ተቃውሞዬን ለእናቴ ብቻ በሚገባ ቋንቋ አልባ ድርጊት እገልጻለሁ:: ጉንጩን እነፋና ትከሻዬን እንደ እስክስታ ወራጅ እሰብቃለሁ:: እሷ ደግሞ "ተው አንተ ልጅ" በማለት ታስጠነቅቀኛለች:: በቆምኩበት እንደጨፋሪ እሰበቃለሁ፣ ከተቀመጥኩም እግሬን እንፈራግጣለሁ::

"እሂሂ! ብታርፍ ይሻልሃል!"

በተቃውሞዬ እፀናለሁ::

"አንተ ልጅ!" ብላ ማማሰያዋን ስትቃጣ ዞር ብዬ አመሰጥኩ:: አባቴ ንትርካችን አልገባውም:: ግር እንዳለው እንግዳውን ይቅርታ ጠይቆ ወደ እናቴ ዞረና "ምን አድርጊ ነው የሚልሽ?"

"ተወው! ተጫወቱ:: እኔና እሱ እንተዋወቃለን" ብላ ወደ እኔ ዞራ "አንተን አያድርገኝ የተያዝክ እንደሆን!"

ከእንግዶቹ አንደኛው በጋሞ ቋንቋ "ምን ፈልጎ ነው?" ሲል ጠየቃት:: 'ምንም!' በሚል ስሜት ትከሻዬን ሰበቅኩ:: አኳኋኔ ግር እንዳለው በመለኪያ የተቀዳለትን ካቲካላ ብድግ አድርጎ ፉት አለና ሞጭሟጫ ዓይኖቹን አስለመለመ:: አባቴም "ተዋቸው እነርሱ ይተዋወቃሉ" አላቸውና ወጋቸውን ቀጠሉ::

እናቴ ዝንጉርጉር ሻሽዋን አጠበቀችና "እግርህን ሳትታጠብ ነው ራትህን የበላኸው?" ብላ መልሴን ሳትጠብቅ ብብትና ብብቴን በእጆቿ ይዛ አነሳችኝና ትልቁ አልጋ ላይ ቁጭ አደረገችኝ:: ከዚያም ለብ ባለ ውሃ እግሬን እየፈተገች "የትም አቧራ ስታቦን ውለህ ምን ምን እንደምትሸት ባወከው? ፈሳም! ያንተን እግር ማጠብ..."

"ወይኔ ቁስሌን!" አልኩና ጮኽኩኝ::

"ዝም በል!" አለና አባቴ ዘሎ መጥቶ አፈጠጠብኝ::

ሕመሜን ዋጥኩ::

"ጋሼ ስታርስልኝ ስትኮቷኩትልኝ ነው እንቅፋቱ የመታህ? ቀጣፊ! እዚህ እኛ የምንጨነቀው ላንተው የወደፊት ኑሮ የተቃና እንዲሆንልህ ነው:: ትሰማለህ? የአያት የቅድመ አያት መሬታችንን በነፍጠኞች እየተነጠቅን ነው" አለኝ በኃይለ ቃል::

አልገባኝም:: የእግሬን ሕመም ቻል አድርጌ ጨዋታቸውን ለማድመጥ ሞከርኩ:: እማዬም ያለምንም ከልካይ እግሬን እንደልቧ መፈተጉን ቀጠለች:: አሙሙኝ ብዬ ብቃወም የሚከተለውን ስለማውቅ ህመሙን ቻልኩት::

እማዬ ብዙውን ጊዜ እግሬን የምታጥበኝ ሌላ የሚያጣድፍ ጉዳይ ሳይኖራት ነው:: ፋታ ካላት አጠገቤ ቁጭ ብላ ስታጠብ እያስተዋለች "ቁርጭምጭሚትህ'ጋ እሸው! የጣቶችህ መሀልና

"ሆድህ ይተርተር በብረት" ብላ ትኮረኩረኛለች፡፡ ፍንድቅ ብዬ እስቃለሁ፡፡ ቂመኝነቴ፣ አልታዘዝም ባይነቴ፣ ማመፁን ይሬ ሳና በሳቅ ጠበል ተጠምቄ ሌላ ልጅ እሆናለሁ፡፡

"ኧረ እዚህ ቁም ነገር ጨዋታ ላይ ነን!" አባቴ ተቆጣ፡፡

"እሺ ተጫወቱ" እማዬ ዝቅ ባለድምፅ መልሳ ለኔ ደግሞ በሹክሹክታ ያህል "አንድ ሰውዬ ነበረ..." ብላ ስትጀምር ትመስ ጠኛለች፡፡ ጠይም ገጽዋ የተቆላ ቡና ይመስላል፡፡ ንቁ ዓይኖ ችዋን ቦዘዝ አድርጋ እያስተዋለችኝ ብዙም ወጣትነት ያልራቀው አካልዋ ዘና ይላል፡፡

አልጋው ጫፍ ላይ ተቀምጣ ኮስተር ብላ አናቴን እየደ ባበለች፣ ወይም ነጠላዋን እየቋጨች፣ አለበለዚያም እየፈተለች ትረካዋን ትጀምራለች፡፡ እማዬ ሁሌም ሁለት ሰው ነች፡፡ እያ ወጋች የምትሠራው ከእጇ አይጠፋም፡፡ ሥራ የምትፈታው ወደ እኩለ ሌሊት አካባቢ የዕለት ሥራዋን አጠናቅቃ ከሁላችንም መጨረሻ ጉንዋን ለማሳረፍ ወደ አልጋዋ ለመተኛት በምት መጣበት ወቅት ብቻ ነው፡፡

በእንዲህ አይነቱ የተረት ሰዓት የምደሰተው እኔ ብቻ ሳል ሆን እማዬም ጭምር ነበረች፡፡ ሳጫውታት፣ ሳደምጣት ደስ ይላ ትና "ጎሽ ፋንጋዬ እየደረስክልኝ ነው" ትልና ለራሷ ያከል በለ ሆሳስ "አምላክ የተባረክ ልጅ ባደረገህ ብቻ" ብላ ታጉተመ ትማለች፡፡

የሕይወቷን ክፍተት እኔ እንድሞላላት አምላክ ስለላከላት ደስ ይላታል፡፡ ደስታዋ ያለአንዳች ቃል፣ በድርጊትዋ ስለሚገባኝ ፍቅራችን ጥልቅና ጥብቅ ነበር፡፡

ብርድ ልብሱን ተከናንቤ፣ ጭንቅላቴን ብቅ አድርጌ በተ ረቱ ውስጥ የሚፈጠረውን ሰውዬ በዓይነ ሕሊናዬ እሥለዋለሁ፡፡ ትዝ እንደሚለኝ በዚያ አይጠገቤ በሆነ የልጅነት ወቅት ያለ ምንም ግርዶሽና ዓይነጥላ በርካታ ተረቶችን ሰምቻለሁ፡፡ አንዳን ዶቹ አሳዛኝ ሲሆኑ፤ የተቀሩት አጨራረሳቸው አስቂኝ፤ አልያም አስፈሪ ይሆኑብኛል፡፡

በተረቱ ውስጥ የሚከሰተው ባሕርይ የተራበ፣ የተጠማ፣ አያሌ ምዕራፎች የተጓዘ የመንግሥት መልእክተኛ ወይም አንድ የራሱ የሆነ ተልእኮ ያለው ሰው ይሆናል፡፡ ሁሌም ሰውዬው ሲታየኝ ሽመልና ስንቅ ይዞ ነበር፡፡

እማዬ ተረቶች ውስጥ ሰውም፣ የዱርና የቤት እንስሳትም አሉበት፡፡ የጦጣን ብልጥነት፣ የዝንጀሮን ቂልነት፣ የአህያን ቻይ ነት፣ የአንበሳን ኃያልነት፣ የነብርን ቁጡነት፣ የዔሊን ቀርፋፋነት ታሳየኛለች፡፡

እኔ አልጋዬን ለእንግዶቼ ለቅቄ አላስተኛም ብዬ እንደ ማምፀው፣ አህያስ ለምን ሰዎችን እምቢ ብሎ ጫካ ውስጥ አይኖርም? ዝንጀሮስ ለምን ብልጥ አይሆንም?... እያልኩ ፅንፍ



አልባ ጥያቄዎችን አነሳለሁ፡፡ እናቴም ሳትታክት ልታስረዳኝ ትሞክራለች፡፡ ከዕውቀቷ በላይ ሲሆን፣ "ይህ የእግዚአብሔር ፋንታ ነው" ብላ ምላሹን ለፈጣሪ ትተወዋለች፡፡

የአያ ጅቦን ተረት በሰማሁ ምሽት በጣም እፈራለሁ፡፡ በዙሪያዬ ያለ ማንኛውም ነገር በፍጥነት ጅብ ሆኖ ይበላኝ ይመ ስል ሁሉንም ነገር በጥንቃቄ አስተውላለሁ፡፡ ስተኛም ብርድ ልብሴን በጭንቅላቴና በአግሬ ወጥሬ እከናነባለሁ፡፡ ትንፋሼን ዋጥ አድርጌ ለመተኛት እሞክራለሁ፡፡ እንቅልፍ በዓይኔ ሳይዞር ብዙ እቆያለሁ፡፡ ፍርሐቴ በጣም ከአየለ ክንብንቤን ሳልገልጥ እማዬን እጣራለሁ፡፡ "ምን ሆንክ?" ትለኛለች በውስጤ የዘራችውን ፍር ሃት ረስታው፡፡

"ፈራሁ!"

"ና! እኛ'ጋ፡፡"

"መብራቱን አብሪዋ!"

"ምን አስፈራህ? ና አይዞህ!" ብላኝ ማብሪያና ማጥፊ ያውን ግርግዳው ላይ በዳበሳ ስትፈልግ ንቁ ጆሮዎቼ ይሰማሉ፡፡

አባቴ በቁጣ "ባይበራስ አትመጣም?" ይለኛል፡፡ በሥራ አካ ላቴ የነገሠውን ፍርሃት ሳይረዳ፤ ጉዳዩን ቢያውቅም በአዋቂ ልብ ግድ የለው፡፡ ሁልጊዜ በብልሃት ሳይሆን በግድ ይህንን ዓለም እንድደፍር ያስገድደኛል፡፡

ማብሪያና ማጥፊያው ቀጭ ሲል አምፖሉ ተግ ብሎ አስፈሪውን ጨለማ ያባርረዋል፡፡ ቤቱ ውስጥ ምንም እንደሌለ ብርሃኑ ቢያበስረኝም፣ እንደፈራሁ ወደ ወላጆቼ አልጋ ራቁቴን እሮጣለሁ፡፡ አባቴ ቀልቦ መካከላቸው ያስተኛኛል፡፡

አያ ጅቦ መካከል የሚተኛን ሰው እንደሚበላ ቢተረክል ኝም፣ አባቴን የሚያሸንፍ ጅብ እንደማይኖር እርግጠኛ ነኝ፡፡ በሁለቱ ሙቀት አካሌ እየቀለጠ ፍርሃቴም ገለል እያለ ሲሄድ እን ቅልፍ ይወስደኛል፡፡ ጠዋት ስነቃ እኔነቴን በግርግዳው ጥግ አገኘዋለሁ፡፡

"እማዬ ማታ መሐል አልነበረም እንዴ የተኛሁት?"

"ነው እንዴ?" በማለት አፏግጣብኝ ተነስቼ ፊቴን እንድ ታጠብ ታዘኛለች፡፡ ልብሴን ለባብሼ በመወዘቻ ውሃዬን ይገፍ ያንን ማታ የሰማሁትን አስፈሪ ተረት ለጓደኞቼ ላወራላቸው እወጣለሁ፡፡

የቴያትር ጥበብ በዞረበት ዝር ያላለችው ይህች የእኔ ገነት ጥበቡን ለእኔ አእምሮ መጥና የተውኔት ስልት ባለው ውበት የማቅረብ ችሎታ ነበራት፡፡

አያ ጅቦን መምሰል ስትፈልግ አንዲት ቡትቶ ታነሳና ተከናንባ በጅብኛ ቋንቋ "እመት ጦጢት፣ እመት ጦጢት፣ እባ ክሽን የእኔ እመቤት ነገ አልቤ የምመልስልሽ አንድ አንኮላ ወተት አበድሪኝ ይላታል፤ እቤቷ ሄዶ፡፡"

ሽመል መዘህ ያባረርከውን እንግዳ አሁን ብታየው ታውቀዋለህ?' ሲል ያልታሰበና ከጨዋታቸው ውጪ የሆነ ጥያቄ ጠየቀው::

"እንግዳው ክው! አለ:: ገበሬውም ወደ መኝታው እያዘገመ 'ትናንት አላስገባም ብለህ ያባረርከኝ ሰው እኔ ነኝ:: ሰመሆኑ ወዳጄ! ምን በደልኩህ? የትስ እንተዋወቃለን? አልያስ ለዚህ በል ተነው ነገ ዓይነምድር ለሚሆን እህል እንዳልካፈልህ ብለህ ነው?...' ብሎ ቢጠይቀው፣ እንግዳው በተግባሩ በጣም አዘነ:: ፀፀቱ ስላሸበረው ተወርውሮ ገበሬው እግር ላይ ድፍት አለና እያለቀሰ ይቅርታ ጠየቀው ይባላል::

"አየሽ እጣኑ ቂርቆስ ሲፈርድበት!" አልኳት በጣም ተገርሜ::

"ታዲያስ! ለዚያውም አፍታም ሳይቆይ:: ቢሞት ይሻለው ነበር::"

"ውነትሽ ነው ድብን ባለ!"

እንዲህ አይነት ስብዕናን የሚቀርፁ ተረቶች በሰማሁ ወቅት እኔም ጨዋ፣ ትሁት፣ ሰዎችን አፍቃሪ ሰመሆን እጥራለሁ:: እዚያው በዚያው ባሕርዬ ተለውጦ መንቀዥቀዤን ተወት አደርግና ረጋ ለማለት እሞክራለሁ:: የትረካው ባሕርያት በሕሊናዬ ውስጥ የራሳቸውን ማኅተም ያኖሩብኛል:: በቆይታ ተፈጥሮ ወደ ለገሰችኝ ባሕርይ የምመለስ ቢሆንም በጊዜው አስተዋይና እመዛዛኝ ሆኜ እታያለሁ::

"የባላገር ሰዎች ሁሉም ጥሩዎች ናቸው!" እልና ቤታችን እንግዳ ሆነው የመጡትን ሰዎች በርህራሄ ዓይን አያቸዋለሁ::

"የአገር ቤት ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ልጆቻቸውም በጣም ጥሩ የተባረኩ ናቸው:: የትላልቅ ሰዎችን እግር ያጥባሉ:: ሲልኩዋቸው ይታዘዛሉ:: ከቤተሰቦቻቸው ጋር ይሠራሉ:: እናም የእኔ ቶንጋ..." ብላ እየደባበሰችኝ "አንተም አድገህ ሰው እንድትሆን ፀጋው ከተለገሰህ እግርህ የሚደርስበት ቦታ አይታወቅም:: ሰው የሚወለድበትን እንጂ የሚሄድበትንና የሚሞትበትን አያውቀውም:: የሰው ልጅ እጣው ሁለት አይነት ነው:: ተጉዞ ሄዶ እንግዳ ይሆናል፤ ወይም እንግዳ ይቀበላል:: ስለዚህ ተጓዦም ተቀባዩም ሰዎች ቅን ከሆኑ፣ ኑሮዋቸው ጥሩና መልካም ይሆናል:: አንተም ኑሮህ የሰመረ ሆኖ ሁሉም ነገር እንዲባረክልህ ጥሩ ልጅ ሁን:: ደግ ሁን" እያለች፣ በሕይወት ተሞክሮ የበሰለ ምክሯን በቅጡ እንደሚገባው እኩያዋ ታወራልኛለች::

የምትለው ሁሉ ባይገባኝም፣ ጥሩ ልጅ መሆን እንደሚናርብኝ እረዳለሁ:: ጥሩ ልጅ ከሆንኩ እግዚአብሔር ያሳድገኛል፣ ትምህርቴንም ይገልጽልኛል፣... እካሌ እየዛለ ሄዶ፣ ድብን ያለ እንቅልፍ ይዞኝ ጥርግ አለ::



# ይህች ምራቅ ሳትደርቅ

"ና! የእኔ ቶንጋ! አረብ ቤት ትሄድና የአራት ፍራንክ ዘይት፣ የሁለት ፍራንክ ጨው፣ አራት ፍራንክ መልስ አለው:: እንካ ስሙኒውን:: ስትመለስ የማደርግልህን አታውቅም! ብርር በል! ቱፍ! (ምራቃቸውን እየተፉ) ይህች ምራቅ ሳትደርቅ ከተፍ በል!" አሉ እማማ ረታሽ::

"እሺ::"

"ቆይ አትንከውከው፤ ምንድነው ግዛ ያልኩህ?"

"የአራት ፍራንክ ዘይት፣ የአራት ፍራንክ ስኳር!"

"ይኸው! አላልኩም:: ይሄ ልበቢስ! ስኳር መቃምዋ ሱስ ሆናብሃለች ማለት ነው? ልብ በልና አድምጠኝ...!" ብለው ያርሙኛል:: ከአፋቸው ነጥቄ "የአራት ፍራንክ ጨው::"

"ኧረ እኔ እልወጣኝም! የአራት ፍራንክ ጨው ምን ላደርግበት ነው? ድግስ የለብኝ!" ብለው እማማ ረታሽ አረሙኝ::

እኔና አብሮ አደጎቼ በሰፈራችን ውስጥ ትላልቅ ሰዎችን አረብ ቤት በመላላክ አገልግሎት መስጠቱ አንዱ የውዴታ ግዴታችን ነበር:: ጎረቤቶቻችን ከእናታችን ማኅፀን ስንወጣ ሁሉ የዓይን ምስክር ናቸው:: እንደ አሳዳጊዎቻችን ስለሚቆጠሩም ከቤታችን ውጪ ሁሉም ትላልቅ ሰዎች በእኛ ሕይወትና ደህንነት ላይ የወላጆቻችንን ያህል የመወሰን መብት ነበራቸው::

ተልከን ስንመለስ ልዩ ልዩ ጉርሻ ይሰጠን ነበር:: መላላኩ ከመደጋገሙ የተነሳ ጉርሻቸው ምን እንደሚሆን ከወዲሁ እናውቀዋለን:: የአንዳንዱ ጉርሻ የሚናፈቅ ነበር:: እማማ አመለወርቅ ከጅሩ ዘመዶቻቸው በሚጭኑላቸው ጥቁር ስንዴ የሚጋግሩት ሙልሙል አሁንም ሳስበው ምራቄን እውጣለሁ::

የኃይሉ ዶሮ እናት እማማ ሸጊቱ በውብ ቋንቋቸው ሲመርቁን እዚያው፣ በዚያው አድገን እንዲታየን እያደረጉ አሹቁን በኪሳችን ያጭቁታል:: እማማ ቀለሚቱ አንጎሏ ከተላላክንላቸው በኋላ ከዕለታት አንድ ቀን የወሰዱብንን የጨርቅ ኳስ ይመልሱልናል::

በእኔና በእማዬ ብቻ የሚታወቅ የጋራ ምስጢር አለን:: ልትልከኝ ስትፈልግ ትጠራኝና መልዕክቱን ነግራኝ "ስትመለስ እማደርግልህን አታውቅም" ካለችኝ ስመለስ በጣም የሚጣፍጠኝን የቅንጬ ፍቅፋቂ እንደምትሰጠኝ አውቃለሁ::

ከሁሉ በጣም የሚደብረኝ *ሃደ በቀሉ'ጋ መላክን ነበር:: ቅቤ ነጋዴ ናቸው:: እማዬ ደንበኛቸው ነች:: አንዳንዴ ከእማዬ ጋር ገበያ ስሔድ የስሙኒ የራስ ቅቤ ትገዛቸውና እኔን መርቀውኝ

---

* ሃደ፤ በኦሮሚኛ እናት::

"ስልጆቼ ስል አችለዋለኋ!" አለች፣ አሁንም እንደ መና
ደድ እየቃጣት" አሉ እማማ በለጡ እየሳቁ::
"ሦስተኛ ሣምንትም ዝም ቢላትስ?"
"መጋዣ ነኝ እንዴ? እህል ብቻ እየበላሁ የምኖረው!?
ወዳጅ እይዝበታለኋ! ብላ ቱግ አለች" ሲሉ እማማ በለጡ፤
ታዳሚው ሁሉ በሳቅ አውካካ::

እማዬ ቡና የጠጣችበትን ስኒ ባዶውን ለእማማ ወርቅነሽ
ለጠቻቸው:: ወርቅነሽ ባለ ቀይ ሻሽ ጠይም ረጅም ሴትዮ
ናቸው:: ቡና ተጠጥቶ ካለቀ በኋላ እድምተኞቹ ስኒያቸውን
ይለጧቸዋል:: እሳቸውም የአተላውን አወራረድ በስኒው ላይ እያ
ስተዋሉ መተንበይ ይችሉበታል:: በዚህ ጊዜ ሁሉም በትኩረት
ይከታተሏቸዋል:: እሳቸው በሌሉ ጊዜ ትንበያቸው እንደሠራም
እንዳልሠራም ትልልቅ ሰዎች ሲጨዋወቱ አዳምጫቸዋለሁ:: አሁ
ንም የእማዬን ስኒ አዩና "አንቺ ትፀንሻለሽ ሴትም ልጅ ትወል
ጂያለሽ" አሏት::

አባቴም "እስኪ እንኪ ወርቅዬ፣ ሲኒው አስረጋዡንም ይና
ገር ይሆን?" አለና ባዶ ሲኒውን ሲያቀብላቸው ቤተኛው እንደገና
ሳቀ::

የተንበረከኩብት መሬት ቆረቆረኝና ስንቀሳቀስ፣ ሚዛኔን
ስቼ አጠገቤ ያለውን ሳፋ ስነካ ተንኳኳ:: እማማ ረታሽ ወደእኔ
ሲዞሩ ተፋጠጥን:: ሳቃቸውን ዋጥ አድርገው ተከሳተሩ:: "በል
ተነስ! ሁለተኛ ከሡልጣን ሱቅ ትገዛና ወየውልህ! ለዛሬው ምሬ
ሃለሁ::! ተነሳሁ:: ከቤት ልወጣ ስል እማዬ እናቷን እየደባበሰች
"ና ፉንጋይ፣ ሃደ በቀሉ'ጋ ሔደህ..."

"ቅቤ!" ብዬ ሳላስበው በሽቄ በጣም ጮኽኩ::

"አንተ ወጠጤ! እከከከከ! ተጎረመስ ማለት ነው?! በል
ውጣና ልምጭ ይዘህልኝ ና!" አሉኝ እማማ ረታሽ:: እየተነ
ጫነጭኩ ስወጣ "ኧረ! ለመሆኑ ስንት እንጀራ ብትበላ ነው
እምዬን ቀና ብለህ የምታያት?!" ሲሉ ይሰማኛል::

አንዲት ቀጭን ልምጭ ይዤ ስገባ እማማ ረታሽ ዓይ
ተውኝ ከትከት ብለው እየሳቁ "አንተ!? ይሄ ልጅ እንዴት
ጠግቧል በቁርቀስ?! አሁን ይህች ለንቋሳ ምንህ ላይ ባሳርፍብህ
ነው የምታምህ? በል ወፈር ያለውን መርጠህ አምጣ!"

አንዴ ቢያሳርፉብኝ ለዘለዓለሙ የሚሸኘኝን መቀርቀሪያ
የሚያክል ቆመጥ ይዤ ገባሁ:: እማማ ረታሽ ጭንቅላታቸውን
ይዘው እየጮኹ "አንተን ገድዬ ከርቸሌ እንድማቅቅ ትፈልጋለህ
እንዴ?" ብለው ሳቁብኝና "በል ለዛሬ ምሬሃለሁ:: ሁለተኛ ስትላክ
እምቢ ትልና ወየውልህ:: በርበሬ አጥኜ ልክ አገባሃለሁ:: በል ና!
እግሬን ሳም! የእናትህንም ሳም!..." ያሉኝን እንዳደረኩ እርቀ
ሰላም ወረደ::



"እንካ ለኔም የአራት ፍራንክ ሳሙና ግዛልኝ:: መርፌም
አስመርቅ፤ ልብ አርግ:: አንቺም ስጪው" አሉና ስሙኒው
ተሰጠኝ:: ከመገረፍ በመዳኔ ደስ እያለኝ የተፏት ምራቅ ሳት
ደርቅ ስመድረስ ወደ ሃደ በቀሉ መደብ በረርኩ::

እየሄድኩ አንድ ነገር ትውስ አለኝ:: ባለ ሁለት ፍራንክ
ሳሙና በዚያን ጊዜ ይሸጥ ነበር:: በአራት ፍራንክ አንድ ሳሙና
ገዝቼ መርፌ ከማስመረቅ፤ በአራቱ ፍራንክ ሁለት ሳሙና ብገዛ
ላቸው እንደሚሻል አሰብኩና ተመልሼ መጥቼ ለእማማ ረታሽ
ነገርኳቸው:: ጨዋታቸውን ቆም አድርገው በትኩረት ካደመጡኝ
በኋላ "ጎሽ የእኔ ልባም! እንዲህ አስተዋይ እንድትሆን ነው የምፈ
ልገው:: ባለሁለት ፍራንኩን ሳሙና መግዛት ያልፈለኩት ለምን
መሰለህ? ሽታው ደስ አይልም:: ስለዚህ ብርርር ብለህ ያልኩህን
ባለአራት ፍራንኩን ግዛልኝና ና!" አሉኝ::

በለመደ እግሬ ፈትለክ አልኩኝ::

ከጉልት ስመለስ ጎረቤቶቻችን ወደየቤታቸው ሄደዋል::
እማዬ ብቻዋን ስኒዎቿን እያጣጠበች ነበር:: አኩርፌ ቅቤዋን
አጠገቧ መሬት ላይ ቁጭ አድርጌላት ልወጣ ስል "ፉንጋይ ና!
ቁርስህን ልስጥህ!?"

ዝም አልኳትና ከቤት ሣሙናውን ሳደርስ ወጣሁ!:
"ምን ቸገረኝ "ለአኩራፊ ልጅ ምሳው ራቱ ነው" ስትል
እሰማታለሁ::

ለምሳ ሳልመለስ ስጫወት ዋልኩ:: መሸት እንዳለ ወደቤት
ተመለስኩ:: በቀዝቃዛ ውሃ ሳልፈራ እግሬን ታጠብኩ:: አልጋዬ
ላይ እንጣጥ ብዬ ወጣሁና ተንበርክኬ ልብሴን አወላለኩ::

"ራትህን ሳትበላ ልትተኛ?!" አለች እማዬ በመገረም::

ቂምጣዬን ሣጥኑ ላይ ጣልኩ:: ሹራቤንም ደገምኩት::
ብርድ ልብሱን ገልጬ ልተኛ ስል "ራትህንማ ሳትበላት አትተ
ኛትም" አለች:: ድምፅዋ የጭንቀት ነበር::

ዝም ብዬ ተከናነብኩ::

"ዋ! ረታሽን ነው የምጠራልህ!"

በፍጥነት ከንብንቤን ገለጥኩና አፈጠጥኩባት:: በቆመች
በት ቁልቁል እያየችኝ "ረታሽ!" ጮክ ብላ ተጣራች::

ዘልዬ ከአልጋዬ ወጣሁና "መጀመሪያ ቁርሴን ስጪኝ!"
አልኳት:: በንዴት እርር ድብን ብያለሁ:: ረታሽን ስር በሰደደ
ሁኔታ ጠላኋቸው::

እማዬ እየሳቀችብኝ ጋቢ ከሣጥኑ ላይ አንስታ አለበ
ሰችኝ:: ጓዳ ገብታ እንጀራውን በሳህን ላይ ቀልላ፣ ብዙ ወጥ
አውጥታበት አመጣችልኝ::

"መጀመሪያ ቁርሴን ብዬሻለሁ?"

"ኤድያ! አትበሳበስብኝ! እኔ ቁርስ፣ ምሳ፣ ራት እያልኩ
ስመድብ አልውልም:: የቻልከውን ያህል ብላ!" አለችና ጠረጴዛው
ላይ ሳህኑን አስቀመጠች:: እንዝርቷን ይዛ ፈንጠር ብላ ተቀምጣ

ሰረቅ አርጋ ታየኛለች፡፡ እኔም እየተነጫነጭኩ ጠመ ልጓሜን መፍታት ጀመርኩ፡፡

## ሰኞ

*"ልጆቻችንን ዓይናቸውን ገልጸው እንዲያልሙ እናስተምራቸው"*
*ስሙን የዘነጋሁት ጸሐፊ*

በልጅነቴ ሰኞ በጣም የምጠላው ቀን ነበር፡፡ በአሁኑ የጉልምስና ዕድሜዬ ላይ ሆኜ "ለምን?" ብዬ ራሴን ስጠይቀው አያሌ ምክንያቶች በሃሳቤ ይመጡብኛል፡፡

ለተማሪ ቅዳሜና እሁድ የእረፍት ቀናት ቢሆኑም፤ ነገር ግን በውስጠ ታዋቂ የሥራ ቀናት ናቸው፡፡ ጀምሬ ያላጠናቀቅኩት ወይም ከነጭራሹ ያልሠራሁት የቤት ሥራ፣ ያልታጠበው የትምሀርት ቤት የደንብ ልብስና ሸራ ጫማዬ፣ ያልተከረከመው ፀጉሬ፣ ያልተቆረጠው ጥፍሬ፣ በወጉ ሳይጠናቀቁ የእረፍት ቀናቱ ካለፉ ጭንቀት፣ መሸበርና በራስ አለመተማመን ያሳድሩብኛል፡፡

አርብ ከሰዓት በኋላ በትምህርት ቤታችን በድራማ፣ በመጻሕፍት ንባብ፣ በክርክርና በልዩ ልዩ ጥበባት የሚያዝናኑን መምህራኖቻችን ዕለቱን ፋሲካ ያደርጉልናል፡፡ ሰኞ ዕለት ግን እንደ ባለዛር ተቀይረው ሥነ ሥርዓት፣ ሞራልና ሕግ ይሆናሉ፡፡ ተግባራቸው ትእዛዝ መስጠትና ደንብን ማስፈጸም ብቻ ይሆናል፡፡

እማዬን ከእንዲህ አይነቱ ስጋት እንድትገላግለኝ በጊዜ ልብሴን እንድታጥብልኝ ከወዲሁ አስታውሳታለሁ፡፡ በበቆሎ ቆሮቆንዳ ሸራ ጫማዬን ፍትግ አድርጌ አጥባለሁ፡፡ እሁድ ማታ አካላቴን እታጠባለሁ፡፡ ጥፍሬንም እከረክማለሁ፡፡ ይሁን እንጂ ሁሌ አይሞላልኝም፡፡ የቤት ሥራዬን አልሠራሁም፡፡ በተጨማሪ ሰኞ ጠዋት የለዘዘውን ልብሴን ለብሼ ወደ ትምህርት ቤት ስሄድ ቅዝቃዜው ጥርሴን ማንገጫገጭ ይጀምረኛል፡፡ ቁርሴም ቅዝቃዜውን የሚያብሰው ይሆናል፡፡ የዚያን ዕለት ፀሐይም ዘግይታ የምትወጣ ይመስለኛል፡፡

ወደ ትምህርት ቤት ስሔድ ታቦት እንደተሸከመ ቄስ አረማመዴ አዝጋሚ ይሆናል፡፡ የቤት ሥራ ሠርቶ የመጣ የክፍሌ ልጅ ካጋጠመኝ ለምኜው በፍጥነት ስገለብጥ የልብሴን ቅዝቃዜም እረሳለሁ፡፡ በወሩ መጀመሪያ ላይ ከሆነ "ቲቸር ጥበበ የወር ደሞዝ አምጡ" ብለዋል ስል አባቴ ገንዘብ ከሌለው አስቀድሜ ባለመናገሬ እየተቆጣ የዚያን ዕለት እንድቀር ያዘኛል፡፡ በዚህ ጊዜ



'እልል በቅምጤ' እልና ደስታዬን ዋጥ አድርጌ ዕለቱን በነፃነት ሰጫወት እውላለሁ፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ብልሃቴ ብዙ ጊዜ ይከሽፋል፡፡ ቤተሰቦቼ የትምህርት ቤቱን ደንብ አሳምረው ስለሚያውቁት ቀደም ብለው የደንቡን አድርሰው "እኔ ትናንት መንገድ ላይ ቲቸር ጥበበን አግኝቼአቸው የወር ደሞዛቸውን ከፍያቸዋለሁ፡፡ ካርኒውን አስታውሰህ አጽፈህ ና!" አባቴ ሲለኝ እጢዬ ዱብ ይልና በልቤ እያነባሁ የዔሊ ጉዞዬን እያያዘዋለሁ፡፡

ተዘጋጅተው የመጡት ተማሪዎች በዕለቱ ተርብ ሆነው ይታያሉ፡፡ ተዝናንተው ይጨዋወታሉ፡፡ አንዳንዶቹ ያወጋሉ፣ ይከራከራሉ፣ ቁመታቸውን ይለካካሉ፡፡ ዓለሙ ሰማይ ልብሱን እንዳያቆሽሹበት እየተጠነቀቀ በክራ ይጫወታል፡፡ (ዓይኖቹ ሰማያዊ ስለሆኑ ነው፤ ዓለሙ ሰማይ የምንለው) መኩዬ ቀጫጫው በሰባራ ምላጭ ጥፍሯን ትከረክማለች፡፡ ሻቃ የገነፈለ እስክርቢቶውን የተበጣጠሰ ቀለም እንዲሰባሰብ ከቀፎው አውጥቶ ይንጠዋል፡፡ በቅጥር ግቢው ጥጋጥግ ፀጉሩን የሚደመድመው፣ የተጨማደደ ልብሱን እየሳበ የሚዘረጋጋው ይስተዋላል፡፡

ሁለት ሰዓት ላይ ደወል ይደወላል፡፡ በየክፍላችን እንሰለፋለን፡፡ ከእኛ ፊት ለፊት፣ ከፍ ባለ ቦታ ላይ የትምህርት ቤታችን ርዕሰ መምህር ቲቸር ጥበበ ይቆማሉ፡፡ ሌሎቹ መምህራኖች በእኛና በርዕሰ መምህራችን መካከል ባለ ክፍት ቦታ ላይ ፊታቸውን ወደእኛ መልሰው በመደዳ በአሳርፍ ይቆማሉ፡፡ ሁሉም በአለባበሳቸው ንፁህ ናቸው፣ ጫማዎቻቸው ያንፀባርቃሉ፣ ፀጉራቸውን ተከርክመዋል፣ ጢማቸውን ተላጭተዋል፡፡

በእኛና በመምህራኖቻችን መካከል ቆሞ የሚያዝን ተማሪ አዝገምጋሚ በሆነ ድምፅ "ሰልፈኛ!" ሲል ነቃ እንላለን፡፡ በድጋሚ "ሰልፈኛ! ተጠንቀቅ" ብሎ ያዘናል፡፡ መምህራኑም ሆኑ ደቀ መዛሙርቱ በተጠንቀቅ እንቆማለን፡፡

"ከንዳ!"

ከፊታችን ባለው የክፍል ጓደኛችን ትከሻ ላይ ቀኝ እጃችንን በመዘርጋት እንከነዳለን፡፡ ከፊታችን የቆሙት የክፍል አለቆቻችን የሰልፉ መስመር ሳይጣመም ቀጥ ብሎ መዘርጋቱን በጭንቅላታችን ውሃ ልክነት ያስተካክላሉ፡፡ መስመር ያዛነፈውን ተማሪ ስም እየጠሩ እንዲስተካከል ያዙታል፡፡

አለቆቹ በቃልና በድርጊት የሚሳተፉበትን ሥራ እንዳጠናቀቁ ፊታቸውን አዙረው በተጠንቀቅ ይቆማሉ፡፡ ይሄኔ ያ የባታሊዮን አዛዥ "አውርድ!" ይላል፡፡ ቀኝ እጃችንን ከጓደኞችን ትከሻ ላይ እናወርድና በአሳርፍ እንቆማለን፡፡

በዚህ ወቅት ሁለት የተመረጡ የሰድስተኛ ክፍል ተማሪዎች ከሰልፈኛው መካከል ወጥተው በወታደራዊ አረማመድ ወደ ርዕሰ መምህራችን ቢሮ ይገባሉ፡፡

"ሰልፈኛ ተጠንቀቅ!" ይላል አዛዣችን፡፡

የማቶቱ በረከት የደረሳቸው የአንዳችን እናት "እትዬ፣ ይተ
ዋቸው ማቶት እየሠሩ ነው" ሲሉዋቸው ተቆጭዋ መለስ ይላሉ::

በእንዲህ መልኩ ግርዶሻችንን እየጣስን ራሳችንን ለመሆን
ዘመኑ እስካለፈ ድረስ ጥረናል:: ዱላውንም እርግማኑንም እየቻ
ልንና በልጅ ልብ እየረሳን::

እኔ ወደ ኃይሉ ዶሮ ቤት አካባቢ መሔድ አዘወትር
ነበር:: ውሮ፣ ሻቃ፣ እና ቀጢሳውም ይመጣሉ:: ኃይሉ ዶሮ
የሥዕል ዝንባሌ ነበረው:: ሲፈልግ ጠረጴዛ፣ ወንበር፣ ጎጆ ቤት
መሣል ይችላል:: እሱ እያሳየን እኛም ለመሥራት እንሞክር
ነበር:: እኔ የሚሰጠኝ የቃል ትምህርት ከተግባር ጋር ታግዞ
ሲገለጽልኝ በቀላሉ ይገባኛል:: ሥዕሉን መሣል ስጀምር ግን ጠረ
ጴዛው ሦስት እግር ይኖረውና አራተኛውን የምስልበት ቦታ ይጠ
በኛል:: ወንበሩም በትክክል የቆመ አይሆንም:: ኃይሉ ካስተማ
ረኝ በአሁኑ ዕድሜዬም በውስጤ የቀረው አሳማንና ጎጆ ቤትን
መሳል ብቻ ነው::

ኃይሉ ዶሮም ጓደኞችን ብቻ ሳይሆን ትእግስት ያለው
የሥዕል መምህራችንም ነበር:: የራሱን ደብተር እየቀደደና እየሰ
ጠን እንድንሥል ደጋግሞ ያሳየናል:: እኛም ደስ እያለን እንሞክ
ራለን:: ለራሱም የተሻለ ሙከራ የሚያደርግበት የሥዕል መማሪያ
መጽሐፍ ነበረችው:: አባቱ አባባ ቱሉ ናቸው የገዙለት:: ኃይሉ
ዶሮ እያሳየን በተመስጦ እንሥላለን:: አንድ ቀን እንዲህ
በመማማር ላይ እያለን እናቱ እማማ ሸጊቱ ወደቤት ሲገቡ
በግዙፉ አካላቸው በሩ ላይ ቆመው ብርሃኑን ከለሉንና "ጉድ!
ጉድ! ታያላችሁ እነዚህ ውጫጮች የሚሠሩትን:: ለካ እንዲህ
እየተሞነጫጨረበት ነው ደብተሩ በሳምንት በሳምንት አለቀ የሚባ
ለው! ግርማ ዝም ብለህ ታያለህ!" ብለው ለዶሮ ታላቅ ወንድም
ቀኝ እጃቸውን ሰጡት::

ሁሌም ጉዳዩን ሳያጣራ እርምጃ በመውሰድ ፈጣን የሆነው
ጎረምሳው ግርማ ቱሉ የሥዕል መማሪያ መጽሐፉን ነጥቆን፣ በሰባ
ተኛ ክፍል እንግሊዘኛው ሙልጭ አድርጎ እየሰደበን፣ በካልቾ
እየለጋ ከቤት አስወጣን::

በሥዕል ጥበብ ዓይነጥላችንን የመግፈፍ ጥረቱም እዚህ ላይ
ቆመ:: የዶሮ ችሎታም ክፍ ሳይል ቀረ::

"ከዛሬ ጀምሮ በደብተራችሁ ላይ ትሞነጫጭሩና ነፍስ-
ሥጋችሁን እለያየዋለሁ!"እያሉእማማ ሸጊቱም አይነ ጥላ ሆኑብን::

'ልጅ አባቱን ይበልጣል' ይባላል:: በዚያን ወቅት በጥበብ
ረቂቅ ምስጢር በመንፈስ ከታላላቆቹ ኢትዮጵያውያን ሠዓሊዎች
አገኘሁ እንግዳ፣ አለፈለገ ሰላም፣ ሜትር አርቲስት አፈወርቅ
ተክሌ እና ከሌሎችም ጋር በምናባችን እያወጋን እንደሆን ማን
ያውቃል 'የልጅ ነገር ሁለት ፍሬ፤ አንዱ ብስል አንዱ ጥሬ'



ይበሉን እንጂ ያበሰልነውን ጥሬ በሚያደርጉብን አዋቂ ሰዎች ላይ
ሳናቂም ወደ ሌላ አይነት ጨዋታ እንሰማራለን::

የክረምት ወቅት ይመስለኛል:: ዘንቦ እንዳባራ በደመና
ግላጭ ፀሐይ ብቅ አለች:: ትንሽ ቆይታ በፀሐይዋ ብርሃን ውስጥ
ካፊያ ጀመረ:: "ውይ ልጆች ይሔኔ እኮ ጅብ ወልዳለች" አለ
ጉቢጥ እንጋጦ እያየ::

"ክርስትና ለእኔ" አለ ቀጢሳው::

በጣም ሳቅን::

ዝናብ እንዳባራ ጭቃ እያቦካን መጫወት ጀመርን:: ጨዋ
ታው በቆይታ እንደ ምርጫችን ይቀየራል:: ቅርፃ ቅርፅ መሥ
ራት ጀመርን ጠረጴዛ፣ ጀበና፣ ስኒ፣ ጎጆ ቤት፣ ሰው:: ሁላች
ንም በየራሳችን ፈጠራ ተመስጠናል:: በዚህ መካከል ውሮ "የሠራ
ሁትን ሰው እዩ" አለና ቀልባችንን ሳበው::

በአጠገባችን አልፋ የምትሄደው መዓዛ ሥራችንን አይታ
"የውሮ ሰው ከሁላችሁም ይበልጣል:: ሸንት መሽኛ ግን የለውም"
አለች::

"እሱንማ በጣም ትልቅ ሠርቼ አሳይሻለሁ" ብሎ ውሮ
ጭቃ አነሳና በትልቁ ማድበልበሉን ጀመረ:: አንድ ቀን የሠራ
ችኝ ተንኮል አሁን ትውስ አለኝ:: እምቢ እንዲላት በጥቅሻ
ስንግረው አየችኝና በኩርኩም ቀጋችኝ! እኔም እየጮኽኩ "ምን
አደረኩሽ? ተይ አንቺ ልጅ! በናትሽ! በጉልበትሽ አምላክ!" እያ
ልኩ ሳለቅስ አባባ አጋፋሪ ሰሙን::

አባባ አጋፋሪ አንድ ዓይና ናቸው:: ለአንድ ዓይናቸው
ሲሉ ዓለምን ሁሉ ይፈራሉ:: መዓዛ ስለመታችኝ ይቆጧታል ብዬ
ስጠብቅ፣ እሳቸው ግን ራሳቸው ጥቃት እንደደረሰባቸው ሁሉ
"ጉድ! ጉድ! እንዲያው የት ብንሄድ ነው በሰላም የምንኖረው?"
ሲሉ ጠየቁ:: ግር አለን:: የባሰ ምን ተፈጠረ? በሚል ስሜት
መጮኼን አቆምኩ::

በአጠገባችን ሲያልፉ የነበሩት አባባ ተሰማ ተገርመው
"ምን ተፈጠረ፣ አጋፋሪ?" አሉ::

"እነዚህ ልጆች አንድ የሚላቸው አጡ'ኮ፣ የገነት አባት::
አታዩም? ይሄ የሚያድበለብሉት እኮ ሰው ለመምታት ነው::
የሰው ዓይን ቢያፈሱስ?"

"አጋፋሪ፣ ያንተ ዓይን ሁሌንም የሚያሳይህ አድቦልቡሉ
ነው? ልጆቹ ለራሳቸው መጫወቻ ዕቃ እየሠሩ ቢጫወቱ ምን
አለበት?" አሉ እማማ በለጡ ገጠ:: ጫጫታውን በርቀት ሆነው
እየተከታተሉ ነበር::

"ወቸው ጉድ! አንቺ ገጣጣ፣ ስድበሽ ለስዳቢ ስጭኛ! ይሄ
ድብልብል አይደለም?!" ብለው በዚያችው አንድ ዓይናቸው አባባ
አጋፋሪ አፈጠጡ::

ማንንም የማይፈሩት እማማ በለጡ ፈገግታ ከፊታቸው
ሳይጠፋ "ተው! ተው! አጋፋሪ:: 'አንድ ዓይና ባፈር አይጫወ

ሸጊቱ:: ትንሽዬዋን ሣይንሣዊ ምርምራችንን በሳንሱር መቀሳቸው እየቆራረጡ እዚያ ላይ አመከኑብን::

የልጅ አእምሮ ንፁህ ነው:: ይሁን እንጂ ቤተሰቦቻችንና ማኅበረሰባችን በየበኩላቸው በባሕርያችን ላይ የራሳቸውን ክንቱነት እያነፁብን ሰብዕናችን መጉደፍ የጀመረው በዚያው በጨቅላነታ ችን ጊዜ ነበር::

የአንዳችን እናት የወሬ ሱሰኛ ይሆናሉ:: ጎረቤትም አላፊ አግዳሚም በክፉ ያነሳኛል ብለው ሁሌም እንደ ጠረጠሩ ነው:: ስለዚህ ልጃቸውን ይጠሩትና "በል ና ቀስ ብለህ የምትጫወት መስለህ እነ እገሊት ምን እንደሚሉ ስማና ና!" ብለው ይልኩታል:: ሰብቀኝነት ገና ከማለዳው በእንዲህ መልኩ በሰብዕ ናው ላይ ተዘርቶ ያድጋል::

"አፈር ያስበላችሁ! የእናንተ እጅ በሶ ጨብጧል? ሳትፈ ነክተው የመጣህ እንደሆነ እዚህች ቤት እንጀራ አትቀምሳትም:: ሞቼ ነው ቆሜ እንዳንተ አይነቱን አጋሰስ የምቀልበው" የተባሉ በዚያው በጨቅላነት ዕድሜ የሂትለር መንፈስ ይጠናወታቸውና እንደ ነብር ደም የጠማቸው ሆነው ወደ ገሃዱ ዓለም ይቀላ ቀላሉ::

የአንዳንድ ወላጆቻችንን ቅድስና ሳስብ ግን የኅብረተሰባች ንንም አስተዋይነት እዚህ'ጋ ማንሳቱ ግድ ነው:: አንድ ያልተለ መደ ወሬ ሳንጠየቅ መተርተር ስንጀምር አፋችን በጥፊ ይጮ ላል:: "ሁለተኛ እንዲህ አይነት ወሬ ታመጡና ወየውላችሁ ዕባኑ ቂርቆስ አይለመነኝ በርበሬ አጥኜ ነው ፊሳችሁን የማስጨር ሳችሁ:: ገና ብቅ ከማለት የምን ወሬ ነው?!" ሲሉን፤ በዕለቱ ያስ ደንግጠን እንጂ ከዓመታት በኋላ ስናስተውለው ታላቅ ፍስሐ የሆነ፤ ዓይነጥላችንን የገፈፈ ፀጋ ኖሯል::

አስተዋይነት ብቻ ሳይሆን ፍቅርም የሚዘራብን ጊዜ ነበር:: "ና የኔ ቶንጋ አደተ አይደል እንዴ? ይሄ ደግሞ ማነው? አቤት ጊዜ እንዴት ይሮጣል!? ይሄ እውነት ውሮ ነው? አሁን ስሙን ማን አላችሁት? አዎን ገነነ ሸጋ ስም ነው:: ና ሳመኛ" ይባልና በፍቅር የምንዋኝበት፣ አብረን የምናወጋበት ሁኔታ ይፈጠራል::

"እስኪ ሬዲዮኑን ክፈቱት:: ቶንጋይ፣ ና ደንስልኝ" እባላ ለሁ:: "ተስፋዬ ነው ስሙ? እውነትም ተስፋዬ::"

መደነስ እጀምራለሁ::

እንዳለመታደል ሆኖ ሬዲዮኑ ዜና ማውራት ይጀምራል:: *"እንደምን ዋላችሁ? ዜናውን የማሰማችሁ ታደሰ ሙሉነህ ነኝ"*

"ቆይ ጥላሁን ገሠሠ መዝፈን ሲጀምር ነው የምትደንስ ልኝ:: ቁም አሁን ወሬውን ይጨርሳል:: አይ ባሎቴ፣ ይሄ ቂልሽ ወሬና ዘፈንም አይለይ?"



*ሬዲዮኑ ርዕሰ ዜናዎችን ማተት ጀመረ:: ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በሜክሲኮ የሚያደርጉትን ይፋ ጉብኝት መጀመራቸ ውን ሮይተርስ የዜና ወኪል ገለጸ::"*

ትልልቆቹ ሰዎች እስከ መፈጠራችን ረሱን:: ወሬያቸው ሁሉ ስለ አባባ ጃንሆይ ሆነ:: ሬዲዮኑ ዜናዎችን እንደጨረሰ፣ ሞቅ ያለ ሙዚቃ ጀመረ:: በቆምኩበት መውረግረግ ጀመርኩ:: ውሮ አብሮኝ ይደንስ ጀመረ:: የአዋቂዎቹ ትኩረት ወደ እኛ ዞረ::

የእኔና ውሮ አካል ገና መጋጋል ሲጀምር መኩዬ ቀጫ ጫው ልቀላቀል ልተው በምትልበት የማመንታት ስሜት ውስጥ እንዳለች ከሙዚቃው በላይ እንድ ድምፅ ጎላና "የጥሩ ዕቃ ሥም ፊሊፕስ!" ብሎ ደመደመ::

"ይሄ ዘፈን እኮ አይደለም:: ቆዩ..." አሉ በፍቅር የቀረቡ ባልቴት:: አቆምን::

ነሸጥ ያደረጋት መኩዬ ቀጫጫው ገፋችኝ:: ቀብ አድርጌ እነኳት:: ይሄኔ ባልቴቷ ገላጋይነት ገቡ:: "ኧረ አትጣሉ:: ምን የሚያጣላ ነገር አለ? ጨዋታው እንደሁ ለሁሉም ይበቃል:: መጣ ላት ክልክል ነው:: መምታትም መመታትም አይቻልም:: በሉ ተስማምታችሁ ተጫወቱ?" ብለው በማለዳ መስማማትን የዘሩብን ነበሩ:: ይህ አይነቱ ደግና የማስተዋል መንፈስ ለኋለኛው ሕይወ ታችን ታላቅ ስንቅ ሆነን::

"እንት አቦሬ አፍ ምናምንቴ! ያንተም ሆነ የእሷ አፍ አር! አር! ይላል:: ሁለተኛ አንድ ነገር ትንፍሽ እንዳትሉ!" የተባሉት አብሮ አደጎቻችን በዚያው የጨቅላነት ዕድሜ ቅስመ ሰባራ፣ በራሳቸው የማይተማመኑ፣ ፈሪዎችና ድንጉጦች ሆነው ማደጋቸው ግን ሳይዘነጋ::

'በሠርቶ አፍራሹ' ፈቃድ አንድ ጥበብ ተከስተልን:: በዚ ያም ፈጠራ የማሰብ መብታችንን የከለከለንን ኅብረተሰብ መቅ ጣትና ማሸበር ጀመርን:: በጥበበኛው ሲሳይ ዝቢጥ መሪነት በጥይት ቀለህ ውስጥ እርሳስ እናቀልጣለን:: እርሳሱን ከቀልሃው ጋር አዋህደን በሚስማር እናጎደጉደዋለን:: በውጪ በኩል በቀልሃው ቂጥ ስር በክርክሩ ላይ ክር እናሥራለን:: በሌላኛው ጫፍ ላይ ሚስማር ይታሠራል:: ፍራንክ ካለን በዱምቡሎ አንድ ፓኬት ክብሪት እንገዛለን:: ካለበለዚያም ከየቤተሰቦቻችን ክብሪት እንመ ነትፋለን:: የተወሰነ የክብሪት ሰልፈር በቀልሃው ውስጥ እንፈረ ፍራለን:: በጥንቃቄ ሚስማሩ ከቀልሃው ጋር ተዋህዶ ከድንጋይ ወይም ከግንብ ጋር ሲላተም አሸባሪ የፈንጂ ድምፅ ያወጣል:: መንደርተኛው ኡኡታውን ያቀልጠዋል:: ሕፃናቱ በአመፁ ልባችን ረክቶ በርካታ ክብሪቶች እንደገና ቀልሃው ውስጥ ጨምረን እንዲ ያንባርቅ እናደርጋለን:: የሲኦል ድምፅ መንደሩን ያናውጠዋል::

